ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነ-ጽሑፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

ድኅረ ምረቃ መርሃ ግብር

# ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ራስ-መር የመማር ብልሃትን ከመተግበር አንጻር የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ያላቸው አመለካከትና አተገባበር ፍተሻ፤ በደቡብ ጎንደር ዞን ሊቦ ከምከም ወረዳ በሚገኙ ሶስት ትምህርት ቤቶች በ9ኛ ክፍል መምህራን ተተኳሪነት።

በ

ይታየው አወቀ

ጳጉሜ 2013 ዓ.ም

ጅማ፣ኢትዮጵያ

# ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ራስ-መር የመማር ብልሃትን ከመተግበር አንጻር የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ያላቸው አመለካከትና አተገባበር ፍተሻ፤ በደቡብ ጎንደር ዞን ሊቦ ከምከም ወረዳ በሚገኙ ሶስት ትምህርት ቤቶች በ9ነኛ ክፍል መምህራን ተተኳሪነት።


በ

ይታየው አወቀ

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነ-ጽሑፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል


በአማርኛ ቋንቋ ማስተማር ለሁለተኛ ድግሪ ከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ


አማካሪ

ጥበቡ ሽቴ (ዶ/ር)

ረዳት አማካሪ

ማንያለው አባተ(ዶ/ር)


ጳጉሜ 2013 ዓ.ም

ጅማ፣ ኢትዮጵያ

## ምስጋና

በመጀመሪያ ይህ ጥናት ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ድረስ የሙያ ፍቅራቸውንና የዕወቀት ፍለጋቸውን በማመላከት፣ፈጣን ምጋቤ ምላሽ እየሰጡ ረቂቁን በተደጋጋሚ በማየትና በማረም ፈጣን መልስና እርማት በመስጠት፣ጥናቱ አሁን የያዘውን ቅርጽ እንዲይዝ በማድረግ ለዚህ ላበቁኝ ለውድ መምህሬና ዋና አማካሪዬ ለጥበቡ ሽቴ (ዶ/ር) እና ለረዳት አማካሪዬ ለማንያለው አባተ (ዶ/ር) ምስጋናየ ከፍ ያለ ነው።

በመቀጠልም ለውዷ ባለቤቴ ለፀዳል አማረ ከጎኔ ሁነሽ ለዚህ ቁም ነገር ስላደረሽኝ ውለታሽን በ‹‹ገነት›› እንዲያደርገው እመኛለሁ። ውዷ ባለቤቴ ከዚህ እንድደርስ ብዙ ደክመሻልና ምስጋናየ ከቃልም በላይ ነው።

በመጨረሻም ለታርቆ፣ ለዮናታን፤ ለእንዳልክ፣ ለታዘብና ለቦጋለ በሀሳብ፣ በቁሳቁስና በገንዘብ እየረዳችሁኝ ለዚህ ስላበቃችሁኝ ኮርቸባችኋለሁ፤ ያለናንተ ድጋፍ ይህ ስራ ከዚህ ደረጃ ላይ መድረስ አይችልም ነበርና ምስጋናየ ከልብ ነው።

# አህጽሮተ ጥናት

*የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ራስ-መር የመማር ብልሃትን ከመተግበር አንጻር የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ያላቸውን አመለካከትና አተገባበር መፈተሽ የሚል ነበር። የጥናቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ መጠናዊ የጥናት ስልትን በመጠቀም ገላጭ እስታቲስቲክስ የጥናት ንድፍ ስልትን ተከትሏል። ለጥናቱ የተመረጡት ሶስት ትምህርት ቤቶች በአመቺ (convenience sampling) የናሙና አመራረጥ ዘዴ ሲሆን የጥናቱ ተሳታፊ መምህራን ደግሞ በጠቅላይ የናሙና አመራረጥ ዘዴን በመጠቀም በደቡብ ጎንደር ዞን፣ በሊቦ ከምከም ወረዳ በአዲስ ዘመን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ በይፋግ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትና በአንቦ ሜዳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2013 ዓ.ም 9ነኛ ክፍልን አማርኛ ቋንቋ የሚያስተምሩ 31 መምህራን ናቸው። የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችም የፅሑፍ መጠይቅና ምልከታ ሲሆኑ በፅሑፍ መጠይቁም ሁሉም ተጠኝዎች ሲሳተፉ በምልከታው ደግሞ ከሶስቱ ትምህርት ቤቶች ሶስተ ሶስት ተጠኝዎች በእጣ ተመረጠዋል። እያዳንዱ ተጠኝም ሶሰት ሶስት ጊዜ ምልከታ ተካሂዷል ይህም ባጠቃላይ ሃያ ሰባት ጊዜ ምልከታ ተካሂዷል ማለት ነው። የፅሑፍ መጠይቅ የማስሞላቱና የምልከታው ተግባር በአጥኝው ተደርጓል። የፅሑፍ መጠይቁን አስተማማኝነት ለማረጋገጥ ከጥናቱ ውጭ በሆኑ 10 የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተፈትሾ ውጤቱም በክሮምባች አልፋ ቀመር ተሰልቶ 0.87 ሁኖ ተመዝግቧል። ይህም ከ0.70 በላይ ስለሆነ ተቀባይነት አግኝቷል። በፅሑፍ መጠይቅ የተሰበሰበው መረጃም በነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ቀመር፤ በምልከታ የተሰበሰበው መረጃ ደግሞ በመቶኛ የስታቲስቲክስ የቅመራ ዘዴን ተግባራዊ በማድረግ የጥናቱ ውጤት ተተንትኗል። ከፅሑፍ መጠይቅ የተገኘው አማካይ ውጤትም 3.34፣ መደበኛ ልይይት 0.55፣ የነፃነት ደረጃ 30፣ የቲ ቴስት ዋጋ 34.56 ሲሆን የጉልህነት ደረጃ ደግሞ 0.00 ሁኗል። የመምህራን አተገባበር ለመፈተሽ ከምልከታ የተገኘው አማካይ ውጤት ደግሞ 63.68% ያህል ተመዝግቧል። የጥናቱ ውጤት ጉልህ መሆኑ፣ በፅሑፍ መጠይቅ የተገኘው አማካይ ውጤት ከመቁረጫ ነጥብ 2.5 በላይ መሆኑና የምልከታው አማካይ ውጤት ከ50 በላይ መሆኑ መምህራን ስለ ራስ-መር የመማር ብልሃት ያላቸው አመለካከት እና አተገባበር አዎንታዊ መሆኑን ለማየት ተችሏል። የአማረኛ ቋንቋ መምህራን በሚያስተምሩት ትምህርት ተማሪዎች ራስ-መር እንዲሆኑ ሲያቅዱ፤ ሲተገብሩም ሆነ ሲገመግሙ እንዲሰሩ ቢያደርጉ ተማሪዎች በሚማሩበት የራስ-መር ብልሃትን እቅድ፣ አተገባበርና ግምገማ የራሳቸውን አስተዋጽኦ ሊያበረክቱ እንደሚችሉ ያሳያል። የተማሪዎችን የራስ-መር መማር ብልሃትን በማሰደግ እና ተግባራትን በራሳቸው እየገመገሙ ድክመትና ጥንካሬያቸውን እንዲለዩ በማገዝ እራሳቸው ተሳታፊ የሚሆኑበትን ምርጫ ቢሰጣቸው የተሻለ ይሆናል። በዚህ ጥናት እና በዚህ ጥናት ባልተዳሰሱ በሌሎች የራስ-መር ብልሃት ላይ ሰፋ ያለ ጥናት ቢካሄድ የመምህራንን አመለካከት ለመጨመርና የተማሪዎችን ችሎታ ለማዳበር የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ቀላል አይሆንም የሚሉት የአጥኝው ጥቆማዎች ናቸው።*

## ማውጫ

ርዕስ ገጽ


ምስጋና ........ i
አህጽሮተ ጥናት ........ ii
ማውጫ ........ iii
የሰንጠረዥ ማውጫ ........ v
ምዕራፍ አንድ፤ መግቢያ ........ 1
1.1 የጥናቱ ዳራ ........ 1
1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........ 4
1.3 የምርምሩ ጥያቄዎች ........ 6
1.4 የጥናቱ ዓላማ ........ 6
1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ ........ 7
1.6 የጥናቱ ወሰን ........ 7
1.7 የጥናቱ ውስንነት ........ 8
1.8 የቁልፍ ቃላት/ ሀረጋት/ አጠቃቀም ውሳኔ ........ 8
ምዕራፍ ሁለት፤ ክለሳ ድርሳናት ........ 9
ንድፈ ሀሳባዊ ዳሰሳ ........ 9
2.1 የራስ-መር መማር ምንነት ........ 9
2.2 የራስ-መር ንድፈ ሀሳብ ፍልስፍናዊ መሰረት ........ 11
2.3 የራስ-መር የመማር ብልሃቶች ........ 13
2.3.1 ተማሪዎች የመማር ግብ እንዲጥሉ ማገዝ ........ 13
2.3.2 የተማሪዎችን የመማር ተነሣሽነትን ማጠናከር ........ 14
2.3.3 የተማሪዎችን የመማር ብልሃቶች ማጎልበት ........ 15
2.4 የራስ-መር መማር አስፈላጊነት ........ 16
2.5 የራስ-መር መማር ተግዳሮቶች ........ 16
2.6 መምህራን ስለራስ-መር መማር ያላቸው አመለካከት ........ 17
2.6.1 የራስ-መር መማር የጥልቀት ደረጃዎች ........ 17
2.7 የራስ-መር መማር አተገባበር ........ 18
2.8 የተዛማጅ ስራዎች ቅኝት ........ 21
ምዕራፍ ሶስት፤ የጥናቱ ንድፍና አካሄድ ........ 24
3.1 የጥናቱ ንድፍ ........ 24
3.2 የጥናቱ አካላይ ........ 24
3.3 የመምህራን ናሙና አመራረጥ ........ 24

3.3.1 የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ....24
3.3.2 የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ....25
3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ....25
3.4.1 የፅሑፍ መጠይቅ....25
3.4.2 ምልከታ....27
3.5 የመረጃ አተናተን ዘዴ....30
ምዕራፍ አራት፤ የጥናቱ መረጃ ትንተና እና ማብራሪያ....32
4.1 የጥናቱ መረጃ ትንተና....32
4.2 የውጤት ማብራሪያ....49
ምዕራፍ አምስት፤ ማጠቃለያ፣ መደምደሚያ እና የመፍትሄ ሀሳብ....52
5.1 ማጠቃለያ....52
5.2 መደምደሚያ....53
5.3 የመፍትሄ ሀሳቦች....53
ዋቢ ፅሁፎች....55
አባሪዎች....

## የሰንጠረዥ ማውጫ

ሰንጠረዥ 4.1 የፅሑፍ መጠይቅ ምላሽ በፐርሰንት የሚያሳይ ሰንጠረዥ............................32
ሰንጠረዥ 4.2 የፅሑፍ መጠይቅ የቲ-ቴስት ውጤት............................................................36
ሰንጠረዥ 4.3 ተማሪዎች በንቃት ወደ ትምህርቱ እንዲገቡ ማነቃቃት መቻሉ.................. 37
ሰንጠረዥ 4.4 ተማሪዎች ጥንካሬያቸውን እንዲለዩ ማድረግ...............................................38
ሰንጠረዥ 4.5 ተማሪዎች ድክመታቸውን እንዲለዩ ማድረግ................................................39
ሰንጠረዥ 4.6 ተማሪዎች ችግራቸውን እንዲፈቱ የተጠቀማቸው ዘዴዎች..........................40
ሰንጠረዥ 4.7 የመማር ኃላፊነታቸው እንዲጨምር ያካናወናቸው ስልቶች..........................42
ሰንጠረዥ 4.8 ተማሪዎች በራሳቸው ፍላጎት ሀሳብ እንዲያፈልቁ የሚያደርገው እገዛ.........43
ሰንጠረዥ 4.9 ለተማሪዎች አዎንታዊ ለሆነ አመለካከታቸው የሚሰጠው ግብረ መልስ......45
ሰንጠረዥ 4.10 ለተማሪዎች አሉታዊ ለሆነ አመለካከታቸው የሚሰጠው ግብረ መልስ......46
ሰንጠረዥ 4.11 ተማሪዎች በመማር ማስተማሩ ወቅት በክፍል ውስጥ የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ በተመለከተ.........................................................................................................47

## ምዕራፍ አንድ፤ መግቢያ

### 1.1 የጥናቱ ዳራ

ተማሪዎች በትምህርታቸው የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ የራሳቸውን የመማር ብልሃትና ስልት መምረጥና መጠቀም ይኖርባቸዋል። ምክንያቱም የቋንቋ መማር ብልሀቶች በተማሪዎች የቋንቋ መማርና አጠቃቀም ላይ አዎንታዊ ተፅእኖ ስላላቸው ነው (Gardneer፣ 1985)። Richards (2003) ገለፃ በመማር ረገድ ተፅእኖ የሚያደርሱ ስነ-ልቦናዊ፣ ማህበራዊ፣ አመለካከታዊ፣ ስብዕናዊ፣ አዕምሯዊ፣ ስነ-ፍጥረታዊ፣ ዝንባሌያዊ፣ ግላዊ፣ ግንባታዊ፣ የመማር ማስተማር ስልትና የብልሃት ምርጫዎች አሉ።

በመሆኑም ተማሪዎች ቋንቋን በመደበኛው ፕሮግራም ለመማር ሲመጡ በቋንቋ ትምህርታቸው ላይ ወሳኝ የሆኑ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተፅእኖዎችን ማሳደር የሚችሉ የየራሳቸውን ግላዊ ባህሪያት፣ ችሎታ፣ የመማር ብልሃትና ግብ ይዘው ነው (Richards፣2003) በተጨማሪም የተማሪዎችን የመማር ምርጫ ልዩነት በተመለከተ ማረው (1990) Rahim (1991) ጠቅሰው እንደገለጹት፡-በተማሪዎች መካከል የስብዕና፣ የማህበራዊ ዳራ፣ የፆታ፣ የእድሜ፣ የመማር ምርጫ ወዘተ (Learing prefernce) ልዩነት እንዳለ ያስገነዝባሉ። ይሁን እንጅ እንደ ፅሐፊው አገላለጽ በርካታ መምህራን ተማሪዎቻቸውን በአንድ ዓይን ስለሚያዩአቸው ልዩነቱን አይቀበሉም።

ማረው (1990) Kryiyakun (1992)፣ Clarck and Stern (1986) ጠቅሰው እንደገለፁት በተማሪዎች መካከል የመማር ብልሃት ልዩነት መኖሩን አመላክተዋል። ለምሳሌ፡- ተማሪዎች ባላቸው የተሰጥኦ ችሎታ (intelligence) ለመማር ባላቸው ፍቃደኝነትና በመማር ብልሃቶች ምርጫ ይለያያሉ። ይብሬ (2008) (Sharon and Elizabeth፣ 2011) ጠቅሰው እንደገለፁት የተወሰኑ ተማሪዎች ራስ-መር የመማር ብልሃትን በተሰጥኦ ሲጠቀሙ ሌሎች ደግሞ በልምድና በመማር ያዳብራሉ። ማረው (1990) Kryiyakun (1992)፣ Clarck and Stern (1986) ጠቅሰው እንደገለፁት በተማሪዎች መካከል የመማር ብልሃት ልዩነት መኖሩን አመላክተዋል። ለምሳሌ፡- ተማሪዎች ባላቸው የተሰጥኦ ችሎታ (intelligence) ለመማር ባላቸው ፍቃደኝነትና በመማር ብልሃቶች ምርጫ ይለያያሉ።

የቋንቋ መማር ብልሃቶችን በተመለከተ ምርምር ማድረግ የተጀመረው እ.ኤ.አ በ1960ዎቹ ገደማ ነው። ይህም ከአዕምሯዊ  የስነ-ባህሪ እድገት ጋር ተያያዞ የመጣ ነው። Pintrich and De goot (1990) እንደገለፁት ሶስት የመማር ብልሃት ምድቦችን አመላክተዋል። እነርሱም

አዕምሯዊ፣ ራስ-መርና የማስታወስ ብልሃቶች ናቸው:: በሌላ በኩል Davies (1999) እንደሚገልጹት በRoben (1987) አከፋፈል መሰረት ተማሪዎች በቋንቋ መማር ወቅት የሚጠቀሙባቸው ሦስት አይነት ብልሃቶች አሉ:: እነዚህም 1ኛ ተግባቦታዊ ብልሃት 2ኛ የመማር ብልሃት 3ኛ ማህበራዊ ብልሃት ናቸው:: ከነዚህ ብልሃቶች ውስጥ የመማር ብልሃትን ስንመለከት መማር አንድ ሰው ያለውን ጊዜና መረጃ በአግባቡ መጠቀምን የሚያሳይ ነው:: ይህም ራስ-መር መማርን የሚመለከት ነው::

ይብሬ (2008) Pintrich (1999) ጠቅሰው እንደገለጹት ደግሞ ራስ-መር የመማር ማዕቀፍ የሚወክለው ስለማወቅና የማወቅ እንቅፋቶችን መለየትን፣ ተነሣሽነትን፣ ሥነ-ባሕሪንና የግብዓት አመራርን የሚይዝ ነው:: የራስ-መር ተግባራት ግብ መጣል፣ ኃላፊነትን መውሰድ፣ ራስን መገምገም፣ ተነሳሽነትና ውጤታቸውን መገምገም የሚሉትን ተዛምዶ ስንመለከት ከቋንቋ ትምህርት ዓላማዎች ጋር ጉልህ ተዛምዶ አላቸው:: የራስ-መር ተግባራት ግብ መጣል፣ ኃላፊነትን መውሰድ፣ ራስን መገምገም፣ ተነሳሽነትና ውጤታቸውን መገምገም የሚሉትን ተዛምዶ ስንመለከት ከቋንቋ ትምህርት ዓላማዎች ጋር ጉልህ ተዛምዶ አላቸው:: እንደ Zimmerman (1989) አገላለፅ በራስ-መር የመማር ሂደት ተማሪዎች የመማር ግቦቻቸውን ይነድፋሉ፤ የመማር ብልሃቶቻቸውን ይመርጣሉ፤ እቅዶቻቸውን ያዘጋጃሉ፤ የመማር ሂደታቸውን ይቆጣጠራሉ፤ የመማር ውጤታቸውንም ይገመግማሉ::

የራስ-መር የመማር ብልሃት አስፈላጊነት ተማሪዎች በትምህርታቸው ውጤታማ እንዲሆኑ መምህራን የተለያዩ የመማር አማራጮችን ማስገንዘብ አለባቸው:: በከፍተኛ ደረጃ ራስ-መር የመማር ብልሃት የሚጠቀም ተማሪ በብቃት ለመማር የሚያስችሉ ልምዶችና ችግር ፈቺ ብልሃቶች ይኖሩታል:: እነዚህ ባህሪያትም መምህራን የሁሉም ተማሪዎች ባህሪያት እንዲሆኑ ይፈልጋሉ:: ራስ-መር የመማር ብልሃት ከትምህርት ቤት ህይወት በኂላ መማር እንዲችሉ እውቀታቸውንና ፍላጎታቸውን ከአንድ ተግባር ወደ ሌላ ተግባር እያሸጋገሩ እንዲጠቀሙ ያስችላል (Paris and paris ፣ 2001)

ተማሪዎች በትምህርታቸው ራስ-መር እንዲሆኑ ለማድረግ መምህራን ስለ ራስ-መር ያላቸው አመለካከት የሚለካው ተማሪዎች ስለ ትምህርታቸው ያላቸውን ጥንካሬ እና ድክመት እንዲሁም በመማር ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመፈታት የሚያስችሉ ብልሃቶችን ማዳበራቸውን ማወቅ ሲችሉ ነው:: ይኸውም መምህራን ተማሪዎች የራሳቸውን መማር ተቆጣጥረው መማራቸውን ሲያረጋግጡ እና ለተግባራዊነቱ ምቹ ሁኔታን ሲፋጥሩ ነው:: በተጨማሪም ደግሞ ስለ ተማሪዎቻቸው ራስ-መር መሆን ያላችው አረዳድና አስተውሎት

ሲጨምር ነው። መምህራን ስለ ራስ-መር ያላቸው አተገባበር የተለያዩ ምሁራን እንሚከተለው ገልፀውታል።

እንደ Davies (1999) ገለፃ ተማሪዎች ተበራተው በራሳቸው ተነሳሽነት ራሳቸውን የቻሉ እንዲሆኑና በትምህርታቸው ራስ-መር ይሆኑ ዘንድ መምህራን ተከታታይነት ያለው ወቅታዊ የሆነ የተማሪዎችን እምነት ደግፎ (አጠናክሮ) በደንብ እንዲሰሩ የሚያስችል አዎንታዊ ምላሽ መስጠት፤ በጣም ቀላል በጣም ከባድ ያልሆኑ ተግባራትን በመስጠት ስኬታማ የሚሆኑባቸውን አጋጣሚዎች ማመቻቸት፤ተማሪዎች ከሚቀርቡላቸው የትምህርት ማቴሪያሎች ውስጥ የራሳቸውን ግላዊ ግንዛቤ የሚያንፀባርቁ ትርጉሞችን እንዲፈልጉ ማድረግ፤ ተማሪዎች ራስ-መር እንዲሆኑ የሞራል ግንባታ መስጠት እና ውስጣዊ ተነሳሽነታቸውን ከፍ ማድረግ እንደሚኖርባቸው ያስገነዝባል። ስለዚህ መምህራን ተማሪዎቻቸውን ራስ-መር እንዲሆኑ በክፍል ውስጥ አስፈላጊ የሆኑ ተግባራትን መከወን ይጠበቅባቸዋል። በተመሳሳይ መንገድ Torrano & Torres (2004) እንዳብራሩት ስለ ራስ-መር አተገባበር በተለያዩ ምሁራን እንደሚገለፀው ለምሳሌ፡- የማንበብ ትምህርት ለማፋጠንና ተማሪዎችን ራስ-መር ለማድረግ የሚከተሉትን የራስ-መር አተገባበር መመሪያዎችን ይጠቅሳሉ።

የመጀመሪያው በቀጥታ ማስተማር (direct teaching) ራስ-መርነትን የመማር ሂደት ለማፋጠን የሚያስችሉ ብልሃቶችን በማብራራት በቀጥታ ማስተማር የሚቻልበትን መንገድ ነው፤ ሁለተኛው ደግሞ ሞዴል (model) ሲሆን ይህ ቀጥተኛ የሆነ የራስ-መር ማስተማሪያ ሥነ-ዘዴ ነው። በዚህም ተማሪዎች የመምህሩን አርዓያ መሠረት አድርገው በራሳቸው እዲሠሩ የሚያስችል አተገባበር ነው፤ ሦስተኛው ደግሞ ልምምድ (practice) በቀጥተኛና በተዘዋዋሪ መንገድ የተለያዩ የመማር ተግባራትን በመማር ማስተማሩ ሂደት ተግባራዊ ማድረግ ሲሆን በመጀመሪያ እያሳዩና እየደገፉ በማለማመድ በኋላ ተማሪዎች ራሳቸውን ችለው እንዲሠሩ ማድረግ ነው፤ አራተኛው ራስን መቆጣጠር (self-monitoring):- ተማሪዎች የተለያዩ ውጫዊና ውስጣዊ ተፅእኖዎችን በመቋቋም ራሳቸውን መቆጣጠር ወይም መምራት ይችላሉ የሚል ሲሆን፤ አምስተኛው ደግሞ ራስን መገምገም (self-evaluation) ተማሪዎች ከተለያዩ ተግባራት በኋላ የራሳቸውን ብቃት በመገምገም የራስ-መር ትምህርት ጠቀሜታን ይገነዘባሉ። እነዚህን ከላይ የተጠቀሱት የራስ-መር አተገባበሮችን መሠረት በማድረግ የራስ-መር ትምህርት በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ማፋጠን እንደሚቻል parviz (2014) ያብራራሉ። ይህ ጥናትም ተማሪዎች ራስ-መር የመማር ብልሃትን ከመተግበር አንፃር የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ያላቸውን አመለካከት እና አተገባበር በመመርመር ላይ ትኩረት አድርጓል።

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ራስ-መር ማለት አንድ ሰው አካባቢን የመረዳትና የመቆጣጠር ችሎታን የሚወክል ነው:: ችሎታው የሚያካትተው ግብ መጣል፣ ራስን መቆጣጠር፣ ራስን ማዘዝ እና ራስን ማነሳሳት ነው:: ተማሪዎች የአዕምሮ ችሎታቸውን ወደ ተግባራዊ ክህሎት የሚለውጡበት የባህሪ ስብስብ ነው:: የሚመነጨው ከታወቁ ተግባራት ግብረ መልሶች ነዉ (Butler፣1998) እና (Zimmerman፣2008) በተመሳሳይ እንደገለጹት ራስ-መር አእምሮን ወደ መማር ክህሎት የመለወጥ ወይም ራስን የመምራት ሂደት ነው በማለት ይገልፃሉ::

ራስ-መር የመማር ብልሃት ይሁነኝ ተብሎ በተማሪዎች የሚመረጥና መማራቸውን ለማፋጠን ወይም ስለቋንቋ መረጃን ለማካተት፣ ለማስታወስ ብሎም በተግባር ለመጠቀም የሚያግዙ ሂደቶች ናቸው (Ells፣1994):: በዚህ የመማር ብልሃትም ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሚማሩበት ጊዜ አራቱን የቋንቋ ክሂሎችና ሁለቱን የእውቀት ዘርፎች ለመማርና ለማሳደግ በሚደረገው ተግባር የሚያጋጥሟቸውን እንቅፋቶች እንዲለዩ፣ ለትምህርቱ ፍላጎትና ተነሳሽነት እንዲኖራቸው እና የሚያስፈልጓቸውን ግብዓት የሚመረጡና የሚያመቻቹ እንዲሆኑ ያስችላቸዋል::

ራስ-መር መማር ፈርጀ ብዙ ተግባር አለው:: ለአብነት አዕምሮን፣ ስሜትን፣ ተግባርን፣ አካባቢን፣ ግብን፣ የመማር ብልሃቶችን፣ ተነሳሽነትን፣ መቆጣጠርንና መገምገምን ያካትታል:: መምህራን ለተማሪዎቹ ምቹ ሁኔታ ከፈጠሩላቸው ተማሪዎች ደግሞ እነዚህን ተግባራት የሚያከናውኑት እውቀትና ክህሎት ለማገኘት ነው:: ራሰ-መር ተማሪዎች ራሰን የመምራት ክህሎትን በማገኘት መማርን ያመቻቻሉ:: (Zimmerman፣1989)::

Chen (2002) እንደገለፁት ራስ-መር የመማር ንድፈ ሀሳብ ከተማሪ ተኮር ትምህርት አሰጣጥ ጋር ተያይዞ የመጣ ነው:: ራስ-መር የመማር ብልሃት ሲሆን ተማሪዎች በራሳቸው ስልትና አቅጣጫ መማር የመቻል ብቃት ነው:: ተማሪ ተኮር ደግሞ የማስተማር አቀራረብ ዘዴ ነው:: መምህራን የማስተማር ዘዴውን ተጠቅመው የራስ-መር የመማር ብልሃቶችን በማጎልበት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ራስ-መር እንዲሆኑ የራሳቸውን መማር እንዲቆጣጠሩ እና እንዲማሩ ማስቻል ነው::

Azlina (2007) በማሊዥያ የምህንድስና የመጀመሪያ ድግሪ ተማሪዎች በእንግሊዘኛ ቋንቋ ትምህርት ራስ-መር የመማር ብልሃት ከመተግበር አንፃር የመምህራን አመለካከትና አተገባበር

በሚል ርዕስ ላይ አጥንተዋል። በጥናቱም መምህራን ስለራስ-መር ያላቸው አመለካከትና አተገባበር አዎንታዊ መሆኑንና በተማሪዎች ውጤት ላይም የጎላ ተፅእኖ እንዳለው ታይቷል። ከፍተኛ ውጤት ያሳዩ ተማሪዎች ዝቅተኛ ውጤት ካስመዘገቡ ተማሪዎች የበለጠ ራስ-መር ሆነው ታይተዋል።

Boekarts (1999) የኮምፒውተር ሳይንስ ተማሪዎች በእንግሊዘኛ ቋንቋ ትምህርት ራስ-መር የመማር ብልሃት ከመተግበር አንፃር የመምህራን አመለካከትና አተገባበር በሚል ርዕስ አጥንተዋል። በጥናታቸው እንደገለፁት መምህራን ስለ ራስ-መር የመማር ብልሃት ያላቸው አመለካከትና አተገባበር አሉታዊ መሆኑን ያመላክታል።

ተሾመ (2008) ተማሪዎች ራስ-መር እንዲሆኑ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ያላቸው አመለካከትና አተገባበር በሚል ርዕስ ባጠናው ጥናት የመምህራን አመለካከትና አተገባበር አሉታዊ መሆኑን አመላክቷል።

ማሪቱ (2010) ተማሪዎች ራስ-መር እንዲሆኑ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ያላቸው አመለካከትና አተገባበር በሚል ርዕስ በአንደኛ ደረጃ መምህራን ላይ ባጠናችው ጥናት የመምህራን አመለካከት አዎንታዊ መሆኑንና አተገባበራቸው ደግሞ አሉታዎ መሆኑን አመላክታለች።

የ Azlina (2007) እና የ Boekarts (1999) ጥናት በራስ-መር የመማር ብልሃት ላይ ጥናት ማካሄዳቸው እና ከቋንቋ የትምህርት ይዘት ውጭ ማጥናታቸው የሚያመሳስላቸው ሲሆን በጥናታቸው ዓላማና በጥናቱ ውጤት ልዩነት አላቸው። የ Azlina ጥናት ከተማሪዎች ውጤት ጋር የ Boekarts ደግሞ ከተማሪዎች የመማር ብቃት ጋር ያለውን ዝምድና የተፈተሸበት ነው።

የ Azlina (2007) እና የ Boekarts (1999) ጥናት ከተሾመ (2008) እና ከማሪቱ (2010) ጥናት ጋር ደግሞ ራስ-መር የመማር ብልሃት ከመምህራን አመለካከትና አተገባበር አንፃር ማጥናታቸው የሚያመሳስላቸው ሲሆን የተሾመና የማሪቱ ጥናት በቋንቋ መምህራን ላይ መሆኑ ከሌሎቹ ጥናቶች ይለያል።

የተሾመ (2008) እና የማሪቱ (2010) ጥናት በቋንቋ መምህራንና በራስ-መር የመማር ብልሃት መሆኑ የሚያመሳስላቸው ሲሆን በጥናቱ ውጤት፣በጊዜና በቦታ ልዩነት አላቸው።

ከሀገር ውስጥም ይሁን ከሀገር ውጭ የተገኙት ጥናቶች የውጤት ልዩነት ታይቷል ፡፡ የተሾመና የ Boekarts የጥናት ውጤት መምህራን ያላቸው አመለካከትና አተገባበር አሉታዊ መሆኑን ያመላከተ ነው፡፡ የማሪቱ ጥናት ደግሞ የመምህራን አመለካከት አዎንታዊ መሆኑንና አተገባበራቸው ደግሞ አሉታዎ መሆኑን አመላክታለች፡፡ የ Azlina ጥናት ደግሞ የመምህራን አመለካከትና አተገባበር አዎንታዊ መሆኑን አመላክቷል፡፡ ይህ ልዩነት መኖር ስለራስ-መር የመማር ብልሃት መምህራን ያላቸው አመለካከትና አተገባበር በውል ያልተፈተሸና በአጥኚዎች መካከል የሀሳብ ክፍተት መኖሩን ያሳያል፡፡ በመሆኑም በርዕሰ ጉዳዩ ላይ ተጨማሪ ጥናት እንደሚያስፈልግ ያሳያል፡፡ ስለዚህ ይህ ጥናት የተስተዋሉትን ማለትም ከመምህራን አመለካከትና አተገባበር ክፍተቶች ለመሙላት በሊቦ ከምከም ወረዳ በሚገኙ በሶስት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 31 የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ያላቸውን አመለካከትና አተገባበር በመመርመር አሳይቷል፡፡

ሌላው የዚህ ጥናት አነሳሽ ምክንያት አጥኚው ባሳለፋቸው አስር የስራ ዓመታት በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የጠባቂነት መንፈስ ያላቸውና ሁሉንም ተግባር ከመምህሩ የሚጠብቁ በራሳቸው ተነሳሽነት ለመስራት ምንም አይነት ፍላጎት የለላቸው መሆኑን በምልከታ ከማረጋገጡም በላይ በእለት ከእለት የስራ ተግባሩ የሚያጋጥመው ችግር በመሆኑ ለዚህ ችግር መፍትሄ ሊሆን የሚችለው መምህራን ስለ ራስ-መር የመማር ብልሃት ያላቸው አመለካከትና አተገባበር በጥናት ቢፈተሽና የመፍትሄ ሀሳብ ቢቀርብ ችግሩ ይቀንሰዋል ብሎ በማሰብ ነው፡፡

## 1.3 የምርምሩ ጥያቄዎች

- ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ራስ-መር የመማር ብልሃትን ከመተግበር አንፃር የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ያላቸው አመለካከት ምን ያህል ነው?
- ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ራሰ-መር የመማር ብልሃትን ከመተግበር አንፃር የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የክፍል ውስጥ አተገባበር ምን ይመስላል?

## 1.4 የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ራስ-መር የመማር ብልሃትን ከመተግበር አንፃር የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ያላቸውን አመለካከትና አተገባበር መመርመር ሲሆን የሚከተሉት ደግሞ ዝርዝር ዓላማዎቹ ናቸው፡፡

➢ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ራስ-መር የመማር ብልሃትን ከመተግበር አንፃር የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ያላቸውን አመለካከት መመርመር፤

➢ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ራስ-መር የመማር ብልሃትን ከመተግበር አንፃር የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሚያከናውኗቸውን ተግባራዊ እንቅስቃሴዎችን መፈተሽ ነው።

## 1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት ቢጠና ዘርፈ ብዙ አገልግሎት ያሉት መሆኑን አጥኝው ያምናል።

➢ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ራስ-መር እንዲሆኑ የራስ-መር የመማር ብልሃት አተገባበርን ከፍ በማድረግ በክፍል ውስጥ የሚሰጡትን ድጋፍ እንዲያስተካክሉ እና ራስ-መር የመማር ብልሃትን በክፍል ውስጥ እንዲተገብሩ ግንዛቤ በመስጠት ተነሳሽነትን ሊፈጥርላቸው ይችላል።

➢ ለመምህራን፡- ተማሪዎቻቸው የራስ-መር የመማር ብልሃት አጠቃቀም በመለየት የትምህርት አቀራረባቸውን፣ የማስተማሪያ መሳሪዎቻቸውን እና የዕለት የትምህርት እቅዶቻቸውን ከራስ-መር የመማር ብልሃት አጠቃቀም ጋር እንዲያዘጋጁ ሊያግዝ ይችላል።

➢ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የራስ-መር የመማር ብልሃትን ሲተገብሩ ተማሪዎች በራስ-መር የመማር ብልሃት በሚማሩበት ወቅት አብዛኛውን የመማር ማስተማር ሂደት በራሳቸው ሐላፊነትና ተነሳሽነት አንዲወጡ ሊያግዛቸው ይችላል።

➢ ለተማሪዎች፡- በክፍል ውስጥ የመማር ማስተማሩን ተግባር በራሳቸው ኃላፊነት እንዲወጡ በማድረግ በትምህርት ቤትም ሆነ ከትምህርት ቤት ውጭ ላላቸው ህይወት በራስ መተማመናቸውን ከፍ ሊያደርግላቸው ይችላል።

➢ በቀጣይ በዚህ ርዕሰ ዙሪያ ለሚሰሩ ጥናቶች እንደ መነሻ ሁኖ ያገለግላል።

## 1.6 የጥናቱ ወሰን

የመማር ብልሃቶች ብዙ ናቸው። ከመማር ብልሃቶች ውስጥ አንዱ ራስ-መር የመማር ብልሃት ነው። ራስ-መር የመማር ብልሃትን በተመለከተ ምሁራን የተለያየ አመለካከት አላቸው። ምክንያቱም የመማር ብልሃቱ ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ብቻ የሚያገለግል ሳይሆን ለሌሎችም የትምህርት አይነቶች እንዲያገለግል ታስቦ የተዘጋጃ በመሆኑ ነው።

ይሁን እንጅ የዚህ ጥናት ትኩረትና ወሰን ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ራስ-መር የመማር ብልሃትን ከመተግበር አንፃር የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ያላቸውን አመለካከት እና

አተገባበር መፈተሽ ነው። ጥናቱ የተካሄደው በደቡብ ጎንደር ዞን በሊቦ ከምከም ወረዳ በሚገኙ ሦስት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ2013 ዓ.ም ዘጠነኛ ክፍልን አማርኛ ቋንቋን በሚያስተምሩ መምህራን ላይ የተወሰነ ነው። እነሱም፡-አዲስ ዘመን፣ይፋግ እና አምቦ ሜዳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ናቸው። አጥኝው ለመረጃ መሰብሰቢያነት የፅሑፍ መጠይቅና ምልከታን ተጠቀሟል።

## 1.7 የጥናቱ ውስንነት

በደቡብ ጎንደር ዞን በሊቦ ከምከም ወረዳ ከሚገኙት አራት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል የጥናቱ መረጃ የተሰበሰበው በሶስት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብቻ ነው። ሁሉንም ትምህርት ቤቶች በጥናቱ ለማካተት የአቅም፣ የጊዜ እና የገንዘብ እጥረት በመኖሩ፤ የፅሑፍ መጠይቁ እና የምልከታው መረጃ በአጥኝው ብቻ መሰብሰቡ አንጻራዊ ውስንነት ይታይበታል።

## 1.8 የቁልፍ ቃላት/ ሀረጋት/ አጠቃቀም ውሳኔ

ራስ-መር /self regulated/ - ተማሪዎች በራሳቸው ስልት እና አቅጣጫ መማር የመቻል ብቃት፣ አመለካከት /aptitude/ -የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተማሪዎቻቸው ራስ-መር እንዲሆኑ ያላቸው አመለካከት ወይም አስተውሎት፤

አተገባበር / practice/-የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተማሪዎቻቸውን በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ራስ-መር እንዲሆኑ ድርጊቶችን የሚከውኑበት ሁኔታ።

## ምዕራፍ ሁለት፤ ክለሳ ድርሳናት

### ንድፈ ሀሳባዊ ዳሰሳ

### 2.1 የራስ-መር መማር ምንነት

Richards (2003) እንዳብራሩት የግንባታዊያን ንድፈ ሃሳብ አቀራረቦች በጋራ የሚስማሙበት ነጥብ እውቀት በሰዎች አዕምሮ ውስጥ ሊገነባ የሚችለው ሰዎች ራሳቸው በእውቀት ግንባታው ላይ በንቃት ሲሳተፉ መሆኑን ያረጋግጣሉ።

ራስ-መር መማር ማለት አንድ ሰው መማርን እንዴት እንደሚማር ያለውን ችሎታ የሚገልፅ ሀረግ ነው። Erick (2011) ይኸውም አንድ ሰው የሚያስፈልጉትን ክህሎቶች የሚማርበትን የተለያዩ መንገዶችን ያካትታል። በአብዛኛዎቹ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ራስ-መር መማር እንደ "የብቻ መማር" ተደርጎ ሲወሰድ የነበረ ቢሆንም የሚከተሉት መገለጫዎች አሉት። የመማር ግቦችን የማስቀመጥ እና ተገቢ የጥናት ብልሃቶችን የማቀድ ችሎታ፤ ከአቻ እገዛን የመሻት እና ግብረ-መልስ ወይም ማረጋገጫ ለማግኘት ተባባሪ መሆን፤ የመማር መሻሻላቸውን ማንፀባረቅና የጥናት ብልሃቶቻቸውን በዛው መንገድ ማስተካከል መቻል ናቸው።

ራስ-መር መማር ማለት አንድ ሰው የሚማርበትን አካባቢ የመረዳት እና የመቆጣጠር ችሎታን የሚወክል ነው። ችሎታው የሚያካትተው ግብ መጣል፣ራስን መቆጣጠር፣ ራስን ማዘዝ እና ራስን ማነሳሳት ነው። ችሎታው የአዕምሮ ችሎታ አይደለም፤ይልቁንም ራስን የመምራት ሂደት ነው። ተማሪዎች የአዕምሮ ችሎታቸውን ወደ ተግባራዊ ክህሎቶች የሚለውጡበት የባህሪ ስብስብ ነው። የእድገት ሂደት ባህሪ ነው። የሚመነጨውም ከታወቁ ተግባራት እና ግብረ መልሶች ነው። Butler (1998)፣ Zimmerman (2002፣ 2008) በተመሳሳይ እንደገለፁት ራስ-መር መማር የአዕምሮ ችሎታ አይደለም የአምሮን ችሎታን ወደ መማር ክህሎት የመለወጥ ወይም ራስን የመምራት ሂደት ነው በማለት ይገልፃሉ።

Zimmerman (1990) እንደሚያስረዱት ደግሞ በራስ-መርነት ውስጥ የሚካተቱት ጉዳዩች በርካታ ቢሆኑም ሶስት ዋና ዋና ጉዳዩችን ጠቁመዋል። እነዚህም የተማሪዎች ስለ መማርና የመማር ችግሮች እውቀት፣ ውስጣዊ ተነሳሽነት እና የመማር ብልሃቶችን ያካትታል። መማር እና የመማር ችግሮችን እውቀት ተማሪዎች ስለ ትምህርታቸው ያላቸውን ጥንካሬና ድክመት እንዲሁም በመማር ወቅት የሚያጋጥሙ ችግሮች ለመፍታት የሚያስችሉ ብልሃቶችን የማወቅ ሁኔታን የሚይዝ ነው። እንደ Zimmerman (2002) ገለፃ በራስ-መር

የመማር ብልሃት ተማሪዎች ጥንካሬና ድክመታቸውን ያውቃሉ፤ ምክንያቱም የሚማሩት እራሳቸው ባስቀመጡት ግብ እና የመማር ብልሃቶች ነው። እነዚህ ተማሪዎች ከግባቸው አንፃር እራሳችወን ይገመግማሉ፤ መሻሻላቸውን ያያሉ፤ መሻሻላቸው ደግሞ እርካታቸውን እና ተነሳሽነታቸውን እንዲጨምር ያደርጋቸዋል።

ውስጣዊ ተነሳሽነት፡- ይህ ፅንስ ሀሳብ ግላዊ መሻሻልን፤ በጥልቀት መረዳትን፤ ከአስቸጋሪ ነገሮች አዲስ አሰራር መማርን እና ስህተቶች አዲስ የመማር አጋጣሚን የሚፈጥሩ መሆኑን የሚያሳዩ ባህሪያት የሚመለከት ነው። ውስጣዊ ተነሳሽነት ከውስጥ የሚመነጭን ግፊት በመማር ተግባራትን በማከናዎን የሚገኝ የተነሳሽነት አይነት ነው። ተማሪዎች የመምህሩ የማስተማሪያ ዘዴ ቢመቻቸውም ባይመቻቸውም ትምህርቱ ፈተና ቢኖረውም ባይኖረውም ከመማር ወደ ኋላ አይሉም። ትምህርቱን በመማርና ተግባራቱንም በማከናወን ይረካሉ። ውስጣዊ ተነሳሽነት ያላቸው ተማሪዎች የሚቀርቡላቸውን የመማር ተግባራት አስቸጋሪ እንኳን ቢሆኑ ተግባራቱን በማከናዎን ይደሰታሉ። አፋዊ ግፊት ሳያስፈልጋቸው ከራሳቸው በሚመነጭ የመስራት ፍላጎት ይኖራቸዋል (Ells 1994)።

የመማር ብልሃቶች፡- ተማሪዎች የመማር ብልሃቶችን ማወቅ፣ ውጤትማ የመማር ስልቶችን መለየት፣ ችግር ፈች ስልቶችን ማወቅ እንደሚጠበቅባቸው የሚያሳዩ ጉዳዩችን የሚመለከት ነው። ስሜነው (200) Chamot (1990)ን በመጥቀስ እንደሚያስረዱት የመማር ብልሃቶች የሚባሉት ተማሪዎች የሚመሰርቷቸው ክህሎቶች ለማሳደግ የሚረዱና በመማር ላይ በቀጥታ ተፅእኖ የሚያሳድሩ ብልሃቶች መሆናቸው ነው።

ሌላው ብያኔ ደግሞ የሚያሳዩት ክህሎትና የመማር ብልሃት የሚባሉት ይሁነኝ ተብለው በተማሪዎች የሚመረጡና መማራቸውን ለማፋጠን ወይም ስለ ክህሎቱ መረጃን ለማካበት፣ ለማስታወስ ብሎም በተግባር ለመጠቀም የሚያግዙ ሂደቶች መሆናቸውን ያሳያል። ስለዚህ በእነዚህ ተመራማሪዎች ገለፃ መሰረት የመማር ብልሃቶች የሚባሉት ተማሪዎች መማራቸውን ቀላል፣ ፈጣን፣ አዝናኝ፣ በራስ የሚመራ፣ ውጤታማና ወደ አዲስ ሁኔታ የሚያሸጋግር ለማድረግ የሚፈፅሟቸው ተግባራት ናቸው በማለት ይገልፃሉ (Ells፣1994)።
እንደ Zimmerman (2002) ገለፃ አንድ ሰው የራሱን የመማር ስርዓት ሊገነባ ይችላል። ይኸውም መማሩን፣ ስሜቱን፣ ተግባሩንና መቆጣጠሩን ሊለማመድ ይችላል። ይህ ራስን የመምራት አቅም ከሌሎች መማርን፣ የመማር ብልሃት ማቀድን፣ ባህሪን መቆጣጠረን ፤ስለ ራስ ማንፀባርቅና ራስን መገምገም እንዲያዳብር ይረዳዋል።

ይብሬ (2008) የ Bandura (1997) እና Zimmerman (1989) በመጥቀስ እንደሚያስረዱት የአንድ ሰው ባህሪው እና አካባቢው የሚነጣጠሉ አይደሉም። ለሰዎች ብቃት መጎልበትም ማህበራዊ ሁኔታ፣ ሞዴል ማግኘት፣ መከረጅ እና በራስ መማር የሚሉ ብልሃቶች ወሳኝ ናቸው። ራስ-መርነትን ለማጎልበት ደግሞ ሶስት ብልሃቶች መጎልበት አለባቸው፤ እነርሱም ግብ መጣል፣ ማቀድና ችግርን እየፈቱ መስራት ወይም ችግር ፈች ብልሃቶች ናቸው በማለት ተመራማሪዎቹ ይገልፃሉ።

## 2.2 የራስ-መር ንድፈ ሀሳብ ፍልስፍናዊ መሰረት

እ.ኤ.አ ከ1980ዎቹ ዓመታት ወዲህ የራስ-መር ፅንስ ሀሳብ በአካዳሚያዊ መማር ውስጥ የተተገበረበት እና በተለያዩ ንድፈ ሃሳባዊ ምልከታዎችም መፈተሽ የተጀመረበት ወቅት ነው። ይሁን እንጅ ራስ-መር መማር ከማህበራዊ ስነ-አዕምሯዊ መማር/ social cognitive learning/ አንፃር ሲታይ ለፅንስ ሀሳቡ የበለጠ አካታች ማብራሪያ ይሰጣል።

ከማህበራዊ ስነ-አዕምሯዊ መማር ምልከታ አኳያ የሰው ልጅ መማር እና ማደግ የተነጣጠሉ ሂደቶች አይደሉም። እኒህ ሂደቶች የተለያዩ የለውጥ ተግባራትን ያልፋሉ። ማህበራዊ ስነ-አዕምሯዊ መማር ምልከታ በጥቅሉ እንደ Bandura (1977) ገለፃ የማህበራዊ ስነ-አዕምሯዊ ንድፈ ሀሳብ / social cognitive theory) በንጥሉ በግለሰቦች ስነ-ልቦናዊ አሰራር ለውጦች ላይ ያተኩራል።

መማር አንድ ሰው ያለውን ጊዜና መረጃ በአግባቡ መምራት የሚችልበትን ሁኔታ የሚያሳይ ሲሆን ይህንን ደግሞ የሚያመላክት ራስ-መር የመማር ንድፈ ሀሳብ ነው። የህ ንድፈ ሀሳብ እየገነነ የመጣው እ.ኤ.አ በ1980ዎቹ ነው። የዚህ እውቀት የመጀመሪያ አመንጭም የስነ-ልቦና ትምህርት ተመራማሪ የሆኑት Zimmerman ናቸው (Eric፣2011) ።

የራስ-መር መማር ንድፈ ሀሳብ እ.ኤ.አ ከ1990ዎቹ ጀምሮ ከባህሪያዊያን ፍልስፍና ወደ አዕምሮያዊያን የትምህርት ፍልስፍና የመጣ ነው። (Chen፣ 2002) ገለፃ ከተማሪ ተኮር የትምህርት አሰጣጥ ጋር ተያየዞ የመጣ ነው። Ali (2011) እንደሚያስረዱት ትኩረት ማግኘት የጀመረው በቅድመ እውቀት ግንባታ ንድፈ ሀሳብ (contstructivism) ነው ሲሉ ይገልፃሉ። Bandura (2001) እንደገለፁት ደግሞ በመማር ተፅዕኖ ምክንያት የመጣ ሲሆን ይህም ተማሪዎች ለራሳቸው መማር ከፍተኛ ኃላፊነት እንዲወስዱ ያደረገ ነው።

ይብሬ Bandura (1989) ጠቅሰው እንደገለፁት ማህበራዊ ስነ-አዕምሯዊ ንድፈ-ሀሳብ በሰብአዊ፣ ስነ-ባህሪያዊ እና አካባቢያዊ ተፅእኖዎች መካከል ምክንያታዊ የእርስ-በርስ ተራክቦን የሚያሳይ ሞዴል ይገልፃሉ፡፡ የ Bandura ንድፈ ሀሳብ በዋናነት ማህበራዊ ግንባታዊያን (social constructivist) ሲሆን ከማህበራዊ ስነ-አዕምሯዊ ንድፈ ሀሳብ ጋር የጋራ የሆኑ አምስት የግንባታዊያን መርሆዎችን አነፃጽሯል፡፡ እነሱም እንደሚከተለው ተገልፀዋል፡፡

የመጀመሪያው የግንባታውያን ቁልፍ መርሆ የሆነው ትርጉም በተማሪዎች ንቁ ተሳትፎ የሚገነባና ሰዎችም አሁን ባላቸው ዕውቀት እና በአዲሱ መረጃ መካከል ስላለው አለመገጣጠም ዕውቅናው (ግንዛቤው) አላቸው የሚል ነው፡፡ በተመሳሳይ መንገድ የማህበራዊ ሥነ-አዕምሯዊ ንድፈ-ሀሳብ እንደሚያምነው ግለሰቦች ለመማርና ለመሻሻል ከአካባቢያቸው አስፈላጊ የሚሉትን መረጃ ይወስዳሉ፤ ስለሆነም ትርጉሙን የመገንባት ተግባር የማያቋርጥ ሂደት ያደርገዋል፡፡

ሁለተኛው የግንባታዊያን መርሆ ደግሞ መማርና ማደግ ማኅበራዊ ተግባራት ከሆኑ በሌሎች ድጋፍ ይጠናከራሉ፡፡ በተመሳሳይ የማኅበራዊ ሥነ-አዕምሯዊ ንድፈ-ሀሳብ መሰረቱን በሦስትዮሽ የሰብአዊ፣ ሥነ-ባሕሪያዊ እና አካባቢያዊ የማያቋርጥ የእርስ በርስ ተፅእኖ ላይ ያደርጋል፡፡

ሦስተኛው እና አስፈላጊው የግንባታዊያን መርሆ ራስ-መርነት በመማር እና በማደግ ሂደቶች ዙሪያ ወሳኝ ሚና አለው የሚለው ነው፡፡ ይህ ፅንሰ ሀሳብ በማኅበራዊ ሥነ-አዕምሯዊ ንድፈ ሀሳብ ጉልህ ድርሻ ያለው ነው፡፡

አራተኛ የሆነው የግንባታዊያን መርሆ ደግሞ የማኅበራዊ ሥነ-አዕምሯዊ ንድፈ-ሀሳብ ዋና መሰረት በሆነው የአዕምሮ አሰራር የተቀናጀ ዕሳቤ ፅንሰ ሀሳብ ላይ ያተኩራል፡፡ በዚህ መርሆ መሰረት ግለሰቦች ምናባዊ ዕሳቤዎች እና ሳይንሳዊ ምክንያት የማድረግ ችሎታ ያላቸው ሲሆን አሁን ካላቸው ዕውቀትም የሌላውን መረጃ ወይም ችሎታ ለይተው መወሰን ይችላሉ፡፡

በመጨረሻም ሁለቱም የግንባታዊያን እና የማኅበራዊ ሥነ-አዕምሯዊ ንድፈ-ሀሳብ እንደሚያምኑበት ግለሰቦች የተለያዩ ሕይወት ስለሚኖሩ እውነታው ግላዊ ትርጉም ያለው እና ግለሰቦች ለተሞክሮዎቻቸው ባላቸው ግንዛቤ ጥገኛ ይሆናሉ፡፡ በሌላ አነጋገር ሰዎች ለእውነታ እና ህልውና ያላቸው ትርጓሜ ከአካባቢያቸው ተፅእኖ ነፃ ሊሆን አይችልም፤

ይልቁንም ከእምነቶቻቸው እና ከቀደምት ተሞክሮዎቻቸው ጋር ጥብቅ ግንኙነት ይኖራቸዋል።

Jordan (2004) እንዳመለከተው በግንባታዊያን አመለካከት እና አንድምታዎቹ በራሳቸው በግንባታዊያን መካከል እንኳ የተለያዩ አመለካከቶች አሉ። በጥቅሉ ይህ የአስተሳሰብ አስተምሮ ተማሪዎቹ የራሳቸውን ዕውቀት ለመገንባት በሚኖረው ንቁ ተሳትፎ ላይ ያደርጋል። ስለዚህ እውነት እና ዕውቀት የሚፈጥሩ (የሚሠሩ) እንጂ የሚታሰሱ አይደሉም። ግንባታዊያን ምልክታቸውን በጥቅሉ ተራክቦ ላይ ሲያደርጉ ማህበራዊ ግንባታዊያን በበኩላቸው ደግሞ ዕውቀት የተግባቦት እና ስምምት ማኅበራዊ ሂደቶች ብቸኛ ውጤት እንደሆኑ ያስረዳሉ።

## 2.3 የራስ-መር የመማር ብልሃቶች

እንደ Swalander (2007) ገለጻ ተማሪዎች በጣም በርካታና የተለያየ የመማር ብልሃትን ለተለያዩ ተግባራት ይጠቀማሉ። ከእነዚህ ውስጥ ልዕለ አእምሮታዊ ብልሃትን የራሳቸውን የመማር ሂደት ለማደራጀትና ለመገምገም ይጠቀማሉ። ስሜት ገሪ ብልሃትን ስሜታቸውን ለመግታት ይጠቀሙባቸዋል። ማህበረሰባዊ የቋንቋ ብልሃቶችን ደግሞ በትምህርት ሂደት ከሌሎች ጋር ተባብሮ ለመስራት ሲጠቀሙባቸው አዕምሯዊ የመማር ብልሃቶችን አዳዲስ ዕውቀቶችን ቀደም ሲል ከሚያውቋቸው ጋር ለማዛመድ ለመተንተንና በአይነት ለማደራጀት ይገለገሉባቸዋል። በአካካሽ የቋንቋ መማር ብልሃቶች በቋንቋው ዕውቀታቸውን ሲጠቀሙ የሚያጋጥማቸውን የመረጃ እጥረት ለማካካስና ክፍተቱን ለመሙላት ይገለገሉባቸዋል።

ራስ-መር የመማር ብልሃት ፈርጀ ብዙ ቢሆኑም በተለያዩ ጥናቶች ተዘውትረው የሚጠኑት የመማር ብልሃት ሦስት ናቸው። እነርሱም፦ ግብ መጣል፣ ተነሣሽነት እና የመማር ብልሃቶች ሲሆኑ እነዚህም እንደሚከተለው በዝርዝር ቀርበዋል።

### 2.3.1 ተማሪዎች የመማር ግብ እንዲጥሉ ማገዝ

እንደ Erick (2011) ግብ ተማሪዎች ከትምህርቱ በኋላ ሊያገኙት የሚጠብቁት ውጤት ወይም ስኬት ነው። ተማሪዎች ራሳቸውን የሚመሩ እንዲሆኑ መምህራን በመጀመሪያ ተማሪዎች ዝርዝር ዓላማዎች ወይም ግቦች እንዲያሰፍሩ ማገዝ ይኖርባቸዋል። ግብ መጣላቸውም የሚማሯቸውን ተግባራት በቀላሉ እንዲረዷቸው ያግዛል። ትክክለኛ ግብም ውስን ወይም ዝርዝር የሚለካ በጊዜ የተገደበ ነው። መምህራንም ተማሪዎች እንዲያቅዱ በማድረግ ራሳቸውን እንዲገመግሙ በማበረታታት ለውጤታቸው እንዲጓጉ በማድረግ ማገዝ ግዴታቸው ነው

በማለት Erick፣ Radar (2005)ን ጠቅሰው ያስረዳሉ። ይህንን ለማድረግም መምህራን መጀመሪያ ተማሪዎች የጣሉትን ግብ መፈተሽና ምክንያታቸውን እንዲጽፉ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። ከጥቂት ቀናት በኋላ የመዘገቡትን ግብ እንደገና እንዲያዩ እና ያልተመቻቸውን እንዲሰርዙ ያደርጋል። በሁለተኛ ደረጃ ግባቸውን ከመማር ማስተማር ሂደቱ ጋር በማዛመድ የጊዜ ሰሌዳቸውን እንዲያጤኑና እንዲያሰፍሩ ያደርጋል። በሦስተኛ ደረጃ ተማሪዎች ግባቸውን ለማሳካት ሊገጥሟቸው የሚችሉ ችግሮችን በመለየት የመፍትሄ ብልሃቶችን እንዲያቅዱ ያደርጋል። በአራተኛ ደረጃ ተማሪዎች ከግባቸው አንጻር የትምህርት ውጤታቸውን እንዲተነብዩ ወይም እንዲገምቱ ያደርጋል። በአምስተኛ ደረጃ ተማሪዎች ወደ ትምህርት ግባቸው እንዲደርሱ በተከታታይ ማበረታታት እና ለድክመቶቻቸው ሁሉ አዎንታዊ ግብረ መልስ ይሰጣል። በመጨረሻ ተማሪዎች እራሳቸውን እንዲገመግሙ ይደግፏቸዋል። ምክንያቱም እያንዳንዱ ተማሪ የተለያዩ የመማር ግብ፣ የመማር ችሎታ እና የግብ ስኬት ጊዜ አለውና መምህራንም ግባቸውን ያሳኩ ተማሪዎች የበለጠ ከበድ ያሉ ግቦችን እንዲጥሉ ማገዝና ከግባቸው ያልደረሱትን ደግሞ ግባቸውን እንደገና እንዲያጠኑ እና እንዲያሳኩ ከፍተኛ ጥረት እንዲያደርጉ ብልሃቶቻቸውን እንዲሳካላቸውም ስላደረጉት ጥረትና ስኬት ሁሉ ያመሰግኗቸዋል። (Erick፣ 2011)።

### 2.3.2 የተማሪዎችን የመማር ተነሣሽነትን ማጠናከር

ስሜነው Gardner (1985)ን ጠቅሰው እንደገለጹት ተነሳሽነት ማለት አንድ ግለሰብ ክህሎትን ለመማር የሚኖረውን ጉጉት ወይም ፍላጎት ፍላጎቱንም ተከትሎ የሚመጣ የመማር ጥረት እንዲሁም የጥረት ወይም የትጋት ውጤት በማግኘት የሚገኝ አንዳች እርካታ መሆኑን ያስረዳሉ። በተጨማሪም ተነሳሽነት ያለው ተማሪ በትምህርቱ ሂደት ውስጥ ተግባራትን ለማከናዎን ብርቱ ጥረትና ያላሰለሰ ተሳትፎ የሚያደርግ ለሚያከናውነው ተግባራትም መልካም አመለካከት ያለው ተብሎ ሊታሰብ እንደሚችል ይገልፃሉ። በተጨማሪም ተነሳሽነት ዓላማን የማሳካት ፍላጎት እና ዓላማውን ለማሳካትም ኃይልን ከፍላጎት ጋር የማጣመር ሁኔታ መሆኑን ተመራማሪዎች ያስረዳሉ። አክለውም ተማሪዎች የመማር ተግባራትን ለማከናዎን ይችሉ ዘንድ መነሳሳት ይኖርባቸዋል። መነሳሳት ለመማር ያለው ፍላጎት እንደ ልዕለ አዕምሯዊ ተግባር ሊቆጠር ይችላል። ይህም የራስ-መር የመማር ሂደት መቆጣጠርን ያበረታታል።

ተማሪዎች ራስ-መር መማርን ከማበረታት አንጻር ቁልፍ የሆነው ተግባር ተነሳሽነት ነው። ይብሬ፣ Lien (1997)፣ Bekartes (1999) እና Erik (2011) ጠቅሰው እንደገለጹት መምህራንም የተማሪዎችን ግቦች መሰረት በማድረግ ደረጃ በደረጃ እንዲማሩ ለማበረታታት የረጅም (ሴሚስተራዊ) እና የአጭር (የዕለታዊ፣ ሳምንታዊ) የጊዜ ዕቅዶችን ማቀድ

ይኖርባቸዋል። ይህ ዓይነቱ የመማር ሂደት የተማሪዎችን ችግር ፈችነት አፈፃፀምና ተነሳሽነት የሚያጠናክር ነው። መምህራን ተማሪዎችን ከጓደኞቻቸው ጋር እያነፃፀሩ በመለካት ተነሳሽነታቸውን መጨመር ይኖርባቸዋል። ከዚህ በተጨማሪም መምህራን የተማሪዎችን ውጤት ብቻ ከማሳየት ይልቅ ጥንካሬና ድክመታቸውን በመጠቀም የማሻሻያ ትምህርት ለመስጠት ማቀድ ይኖርባቸዋል። የሚሰጣቸው አስተያየቶችም በዕውቀት እና በክህሎት ያደረጉትን መሻሻል መጠቆም አለበት። የሚሰጣቸው ግብረ መልስ ማተኮር ያለበትም መሻሻላቸው ከጥረታቸው ጋር በቀጥታ የተያያዘ መሆኑን ነው። በመጨረሻም የሚማሯቸውን ትምህርቶች ከዕለታዊ የሕይወት ገጠመኝ ጋር በማገናኘት መምህሩም በእውነተኛ ሕይወታቸው ችግር ሊፈቱበት የሚችሉባቸውን የቤት ሥራዎችን እና ተግባራትን ማዘጋጀት የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎችን በመጠቀም ተነሳሽነታቸው እንዲያድግ ማድረግ ይኖርበታል።

### 2.3.3 የተማሪዎችን የመማር ብልሃቶች ማጎልበት

ተማሪዎች በርካታ የተለያዩ የመማር ብልሃቶችን ለተለያዩ ተግባራት ይጠቀማሉ። ከነዚህ ውስጥ ልዕለ አዕምሯዊ ብልሃቶችን የራሳቸውን የመማር ሂደት ለማደራጀት፣ ለመለየትና ለመገምገም ይጠቀማሉ። ስሜት ገሪ ብልሃቶችን ስሜቶቻቸውን ወይም ዝንባሌዎቻቸውን ለመግታት ይጠቀሙባቸዋል። ማህበረሰባዊ የክህሎት ብልሃቶችን ደግሞ በትምህርት ሂደት ከሌሎች ጋር ተባብሮ ለመስራት ሲጠቀሙባቸው ከአዕምሯዊ የመማር ብልሃቶች አዳዲስ እውቀቶችን ቀደም ሲል ከሚያውቋቸው ጋር ለማዛመድ፣ ለመተንተን እና በአይነት በአካካሽ የክህሎት መማር ብልሃቶች በክህሎቱ እውቀታቸውን ሲጠቀሙ የሚያጋጥማቸውን የመረጃ እጥረት ለማካካስና በማደራጀት ይገለገሉባቸዋል። ክፍተቱን ለመሙላት ይገለገሉባቸዋል (Zimmerman፣2008)።

የተሻለ ችሎታ ያላቸው ተማሪዎች ዝቅተኛ ችሎታ ካላቸው ተማሪዎች በተሻለ በርካታ የመማር ብልሃቶችን ለተለያዩ ተግባራት ሲጠቀሙ ማስተዋሉን፤ የመማር ብልሃቶችን አጠቃቀምና ችሎታ መካከል ያለውን ተዛምዶ ውስብስብ መሆኑን እና በሁሉም ደረጃ ያሉ ተማሪዎች የመማር ብልሃቶችን መጠቀማቸውን ይገልፃል። በተጨማሪም እጅግ በጣም በትምህርታቸው ውጤታማ የሆኑ ተማሪዎች ለትምህርቱ በቀረበው ቁሳቁስ፣ መልመጃ፣ ለራሳቸው ግብ ፍላጎትና የመማር ደረጃ ተስማሚ የሆኑ የመማር ብልሃቶችን በተደጋጋሚ እንደሚጠቀሙ ያስረዳል (Zimmerman፣2002) ።

## 2.4 የራስ-መር መማር አስፈላጊነት

ተማሪዎች በትምህርታቸው ውጤታማ ይሆኑ ዘንድ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተለያዩ የመማር አማራጮችን ማስገንዘብ አለባቸው፡፡ ጥሩ ራስ-መር ተማሪ በብቃት ለመማር የሚያስችሉ ክሂሎች፣ ልምዶች እና ችግር ፈች ብልሃቶች ይኖሩታል፡፡ እነዚህ ባህሪያትም የሁሉም ተማሪዎች ባህሪያት እንዲሆኑ መምህራን ይፈልጋሉ፡፡ ራስ-መር የመማር ብልሃትንም ተማሪዎች በህይወት ገጠመኞቻቸው ከትምህርት ቤት ህይወት በኋላ መማር እንዲቀጥሉ ወይም እንዲችሉ እውቀታቸውን፣ ክህሎታቸውንና ብቃታቸውን ከአንድ ጉዳይ ወይም ተግባር ወደ ሌላ እያሸጋገሩ እንዲጠቀሙ ያስችላቸዋል Paris and paris (2001)፡፡ በመሆኑም ብቃቱ ለመማር እጅግ አስፈላጊ ነው ማለት ይቻላል፡፡

## 2.5 የራስ-መር መማር ተግዳሮቶች

መምህራን ተማሪዎቻቸውን ራስ-መር እንዲሆኑ ለማስቻል በሚያደርጓቸው ተግባራት በርካታ የተለያዩና እና ፈታኝ ተግዳሮቶች ያጋጥሟቸዋል፡፡ Bandura (2001) እንደገለጹት መምህራን ተማሪዎቻቸውን ራስ-መር እንዲሆኑ በሚያደርጉት ጥረት የሚከተሉት ተግዳሮቶች /እክሎች/ ይገጥሟቸዋል፡፡ ከነዚህ ተግዳሮቶች መካከል የመጀመሪያው ተማሪዎቻቸው ለመደበኛ ትምህርት ዝግጁዎች አለመሆናቸው ነው፤ ሁለተኛው ተማሪዎች አዳዲስ የመማር ዘዴዎችን ለመቀበል ወይም ስለ መማር ያላቸውን አመለካከት ለመለወጥ ዳተኞች መሆናቸው፤ ሶስተኛው አብዛኛዎቹ ተማሪዎች በመምህሮቻቸው በትክክል የተዘጋጁ የመማሪያ ቁሳቁሶችንና ብልሃቶችን እናገኛለን እናም ፈተናዎችን በቀላሉ በማለፍ የሚፈለገውን ደረጃ እናገኛለን ብለው መጠበቃቸው፤ አራተኛው ቅይጥ የመማር ክህሎቶች ( በከፍተኛ እና ዝቅተኛ ራስ-መር መማር ክህሎት መካከል ያሉ) ያሏቸውን ተማሪዎች እንደ ቡድን ማነሳሳት በራሱ ፈታኝ መሆኑ፤ አምስተኛው ጥቂት የራስ-መር መማር ክህሎቶች ያሏቸው ተማሪዎች መረጃዎችን ከራሳቸው ጋር ለማዋሀድ ወይም አዳዲስ የመማር ዘዴዎችን ለማግኘት ረዥም ጊዜ መውሰዱ እና ይህ ሁኔታም መምህሩ ሁሉንም ክፍል ውስጥ የሚያስፈልጉትን የመማር ክህሎቶች ለማሟላት የሚደረገውን ጥረት ከፍ እንዲል ማድረጉ፤ ስድስተኛው መምህራን ራሳቸው ራስ-መር መማርን ለመከወን የሚያስችል በቂ ስልጠና፣ ሞያዊ ተሞክሮ ወይም ግላዊ የራስ መተማመን አለመኖር እና በመጨረሻም ስርዓተ-ትምህርቱ በራሱ በአንድ የትምህርት አይነት ተማሪዎች ምን እና እንዴት መማር እንዳለባቸው በከፍተኛ ሁኔታ የሚገድብ መሆኑ መምህራን ለተማሪዎቻቸው የራስ-መር መማር ክህሎትን ለማስጨበጥ በሚያደርጉት ጥረት የሚገጥሟቸው ችግሮች እንደሆኑ ገልፀዋል፡፡

## 2.6 መምህራን ስለራስ-መር መማር ያላቸው አመለካከት

በብዙ ሀገራት በተለያዩ ደረጃ ባሉ የትምህርት ተቋማት የሚያስተምሩ መምህራን ስለ ራስ-መር ግንዛቤ አላቸው Chen (2002):: ራስ-መር መማር ለእራሳቸውና ለተማሪዎቻቸው ስለሚያበረክተው ሚና እና ጥቅም ዕውቅናው አላቸው። አንዳንዶች ራስ-መር መማር ብስለትን በማምጣት የአንድ ተማሪ የመማር ኃላፊነት ከፍ እንዲል ያደርጋል ሲሉ ያምናሉ። አክለውም ራስ-መር መማር የተማሪዎችን ለብቻ የመማር ችሎታ ከፍ በማድረግ እና በራስ መተማመናቸውን በመገንባት የተሻሉ ውጤቶችን እንዲያመጡ ያስችላቸዋል ይላሉ። ራስ-መር መማር ተማሪዎች በፍጥነት እንዲማሩ ተፅእኖ ያደርጋል። የተማሪዎችን በንቃት የማሰብ ክህሎትን ያነቃቃል፤ ተራክቧቸውን በማሻሻል በፍጥነት እንዲማሩ ያስችላቸዋል። ሌሎች መምህራን ራስ-መር መማር የተማሪዎቻቸውን ምክንያት የመጠየቅ ችሎታ እንዲሁም አዕምሯቸውን የማሰባሰብ ኃይላቸውን በማሻሻል የተሻለ እንዲማሩ ያደርጋቸዋል ብለው ያምናሉ። መምህሩ ራስ-መር መማር ስልትን በመጠቀም ተማሪዎቹን ወደ ተገቢውና ትክክለኛው መንገድ በመምራት ተማሪዎች ሁሉን አቀፍ እድገት እንዲኖራቸው ያስችላል፤ ይኸም የሁሉም መምህራን ሐላፊነት ሊሆን እንደሚገባው ይመክራሉ Chen (2002)::

Eric (2011) ባደረገው ጥናት መምህራን በመማር ማስተማር ሂደት ራስን የመምራት ሂደት ቁልፍ ሚና እንደሚጫወቱ እንደተገነዘበ ገልጿል። በዚህም ተማሪዎች ድክመታቸውን እንዲያዩ ከማድረጉም በላይ የሚጠቀሙባቸውን የመማር ብልሃቶች ውጤታማነት በአግባቡ እንዲያዩ ያግዛቸዋል ብለዋል። ተማሪዎች እራሳቸውን እንዴት እንደሚመሩ፣ የመማር ብልሃቶችን እንዴት እንደሚመርጡ፣ ራስን የመምራት ክሂሎችንና ብልሃቶችን በተመለከተ መምህራን በቀጥታ በተግባር አስደግፈው እንደሚያስተምሩና ውጤቱን በመገምገም፤ ከውጤቱ በመነሳትም ብልሃቶችን እንደሚያሻሽሉ አክለው መናገራቸውን ገልጸዋል።

### 2.6.1 የራስ-መር መማር የጥልቀት ደረጃዎች

መምህራን የተማሪዎቻቸውን የራስ-መር የመማር ጥልቀት በተመለከተ በሶስት ደረጃዎች ይከፍሏቸዋል። እነርሱም፡-

የመጀመሪያው ከፍተኛ ራስ-መር ደረጃ ያላቸው ተማሪዎች እነርሱም በሳል፣ለመማር ከፍተኛ ፍላጎት የሚያሳዩ፣ ብርቱናየራስ ተነሳሽነት ያላቸው፣ ራሳቸውን ከወቅቱ ወይም ከጊዜው አጣጥመው ወይም አዋህደው የሚሄዱ፣ በቤተ ሙከራና በገለፃ ወቅት ፈታኝ እና የተራቀቁ ጥያቄዎችን የሚጠይቁ፣ ተፈጥሯዊ ችሎታዎች ያሏቸው እና የመማር ተሞክሮዎቻቸውን ለማጎልበት የተሰጣቸውን ሁሉንም አቅርቦት የሚጠቀሙ ናቸው።

ሁለተኛው ደግሞ ዝቅተኛ የራስ-መር መማር ደረጃ ያላቸው ተማሪዎች ሲሆኑ እነዚህም ልጅነት የሚያጠቃቸው ኃላፊነት ለመሸከም ዝግጁ ያልሆኑ፣ ለትምህርታቸው ብዙም ጥረት የማያሳዩ፣ ምንም አይነት ተነሳሽነት የሌላቸው፣ የትምህርት ክትትል የማያደርጉ ጥያቄዎቻቸውን ቀላልና የማይመጥን ደረጃ ያላቸው የሆኑ እና የሚሰጣቸውን የመማር ተግባራትና አቅርቦት በአግባቡ ከማከናወን ይልቅ የሌሎችን እገዛ ሙሉ በሙሉ የሚሹ ወይም የሌሎች ተማሪዎችን ስራ የመገልበጥ ባህሪ ያላቸው ተማሪዎች ናቸው።

ሦስተኛው ቅይጥ የራስ-መር ደረጃ ያላቸው ተማሪዎች ከላይ የተገለፁት ባህሪያት በከፊል የሚታይባቸው ቢሆኑም መገለጫቸው የተለያዩ ተግዳሮቶች ያሉባቸው አይነት ተማሪዎች መሆናቸው ነው። ይኸውም በተለይ እንደ ዝቅተኛ ራስ-መር መማር ተማሪዎች ባይሆኑም ኢ-ጥገኛ ለመሆን እገዛን፣ መበረታታትንና መመራትን የሚሹ አይነት ተማሪዎች መሆናቸው ነው። የህንን መሰረት በማድረግ መምህራን ከፍተኛ የራስ-መር መማር ደረጃ ያላቸውን ተማሪዎች ማስተማር ይመርጣሉ። ለዚህም ምክንያታቸውን ሲገልፁ እንዲህ አይነት ባህሪያት ያላቸውን ተማሪዎች ማስተማር፡- ተማሪዎች በትጋት በመማር ተግባራት ሲሳተፉ ማየት ስለሚቻል እና ተማሪዎች ጠንካራ ጥያቄዎችን ይዘው ስለሚመጡ እና ይህም ለመምህራን ራሳቸውን የሚፈትሹበት መልካም አጋጣሚ ስለሚፈጥርላቸው ነው ይላሉ።

በመሆኑም መምህራን ተማሪዎቻቸውን ከፍተኛ ራስ-መር መማር ደረጃ በመድረስ የተሻለ የመማር ክወና፣ ውጤታማ እና እንከን አልባ እንዲሆኑ ተግተው መስራት እንዳለባቸው (Alexander ፣2007) ይገልፃሉ።

## 2.7 የራስ-መር መማር አተገባበር

ራስ-መርነት በትምህርት ሥራ በጣም አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም ተማሪዎች ከትምህርት ቤት ሕይወት በኋላ ራሳቸውን በትምርት ለማሻሻል ወሳኝ መሣሪያ ስለሆነ ነው። ራስ-መር መማርን ስለሚሰጠው ጥቅም ስሜነው (Dunbar፣ 2010፤ Nash፣ 2010፤ SIwalander and Tobi፣ 2007) ጠቅሰው እንደገለፁት መምህራን ከተማሪዎቻቸው ጋር ስለሚያደርጓቸው ተራክቦዎች ፍንጭ ይሰጣል። ተማሪዎች ቅፅበታዊ በሆነ መልኩ ራስ-መር አይሆኑም። የራስ መርነት ችሎታም በአንድ ጊዜ የሚያጎለብቱት አይደለም (Lapan፣ 2008)። በሌላ አገላለጽ ራስ-መር መማርን የሚያስተምሩት ተግባር ሲሆን የተማሪዎችን ውጤት እንዲሻሻል ያደርጋል Abrami (2010) (Mer Hassen፣ Akbarin and Dihegan፣ 2007)። ጠቅሰው እንደገለፁት ተማሪዎች ራስ መርነትን በክፍል ውስጥ እንዲተገብሩ

ምርጫዎች ሊሰጣቸው ይገባል፤ ይህም የሚሆነው ተዛማጅ ተግባራትን እና ድርጊቶችን በቀጥታና በተዘዋዋሪ መንገዶች እንዲሠሩ በማድረግ ነው።

መምህራን ስለራስ-መር ያላቸውን አተገባበር የተለያዩ ምሁራን እንደሚከተለው ገልፀውታል። Davies (1999) እንደገለፀው ተማሪዎች ተበራተው በራሳቸው ተነሳሽነት ራሳቸውን የቻሉ ራስ-መር ይሆኑ ዘንድ በመምህሮቻቸው ተከታታይነት ያለውና ወቅታዊ የሆነ የተማሪዎችን እምነት ደግፎ (አጠንክሮ) በደንብ እዲሰሩ የሚያስችል አዎንታዊ ምላሽ መስጠት፣ በጣም ቀላል፣ በጣም ከባድ ያልሆኑ ተግባራትን በመስጠት፤ ስኬታማ የሚሆኑባቸውን አጋጣሚዎች ማመቻቸት፤ ተማሪዎች ከሚቀርቡላቸው የትምህርት ቁሳቁሶች ውስጥ የራሳቸውን ግላዊ ግንዛቤ የሚያንፀባርቁ ትርጉሞችን እንዲፈልጉ ማድረግ፤ ተማሪዎቹ ራስ-መር እንዲሆኑ የሞራል ግንባታ መስጠት እና ውስጣዊ ተነሳሽነታቸውን ከፍ ማድረግ እንደሚኖርባቸው ያስገነዝባል። ስለዚህ መምህራን ተማሪዎቻቸው ራስ-መር እንዲሆኑ በክፍል ውስጥ አስፈላጊ የሆኑ ድርጊቶችን መከወን ይጠበቅባቸዋል።

ተማሪዎች በትምህርታቸው ውጤታማ ይሆኑ ዘንድ መምህራን የተለያዩ የመማር አማራጮችን መገንዘብ እና ለተግባራዊነቱም ሳይታክቱ መሥራት ይጠበቅባቸዋል።

በተመሳሳይ መንገድ Torrano and Torres (2004) እና Lapan (2008) እንደገለፁት ስለራስ-መር አተገባበር በተለያዩ ሙሁራን እንደሚገለፀው ለምሳሌ የማንበብ ትምህርትን ለማፋጠን እና ተማሪዎችን ራስ-መር ለማድረግ የሚከተሉት አምስት የራስ-መር አተገባበር መመሪያዎችን ይጠቅሳሉ።

የመጀመሪያው በቀጥታ ማስተማር (direct teaching) ራስ-መርነትን የመማር ሂደት ለማፋጠን የሚያስችሉ ብልሃቶችን በማብራራት በቀጥታ ማስተማር የሚቻልበትን መንገድ ነው።

ሁለተኛው ደግሞ ሞዴል (model) ሲሆን ይህ ቀጥተኛ የሆነ የራስ-መር ማስተማሪያ ሥነ-ዘዴ ነው። በዚህም ተማሪዎች የመምህሩን አርዓያ መሠረት አድርገው በራሳቸው እዲሠሩ የሚያስችል አተገባበር ነው፤ ሦስተኛው ደግሞ ልምምድ (practice) በቀጥተኛና በተዘዋዋሪ መንገድ የተለያዩ የመማር ተግባራትን በመማር ማስተማሩ ሂደት ተግባራዊ ማድረግ ሲሆን በመጀመሪያ እያሳዩና እየደገፉ በማለማመድ በኋላ ተማሪዎች ራሳቸውን ችለው እንዲሠሩ ማድረግ ነው፤ አራተኛው ራስን መቆጣጠር (self-monitoring):- ተማሪዎች የተለያዩ ውጫዊና ውስጣዊ ተፅእኖችን በመቋቋም ራሳቸውን መቆጣጠር ወይም መምራት ይችላሉ የሚል ሲሆን፤ አምስተኛው ደግሞ ራስን መገምገም (self-evaluation):- ተማሪዎች

ከተለያዩ ተግባራት በኋላ የራሳቸውን ብቃት በመገምገም የራስ-መር ትምህርት ጠቀሜታን ይገነዘባሉ፡፡ እነዚህን ከላይ የተጠቀሱት የራስ-መር አተገባበሮችን መሠረት በማድረግ የራስ መር ትምህርት በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ማፋጠን እንደሚቻል parvize (2014) ያብራራሉ፡፡

ራስ-መርነት ተማሪዎች የራሳቸውን መማር አንቀሳቃሽ አካል እንዲሆኑ የሚያግዝ፣ በአነቃቂ እና ገንቢ የመማር ሂደት እንዲሳተፉ የሚያስችላቸው ተጨባጭ እና ተተግባሪ የማስተማሪያ ዘዴ ነው፡፡ ስለሆነም የተማሪዎችን ራስ-መርነት ችሎታ ከፍ ለማድረግ መምህራን ሊተገብሯቸው የሚገቡ አራት የማስተማር ደረጃዎችን ZImmerman (1990) አዘጋጅተዋል፡፡ የመነሻ ራስ ቁጥጥር (Benchmark Self Monitering)፣ የተዋቀረ (structured) የብቻ ራስ ቁጥጥር (Independent) ራስ ቁጥጥር እና የራስ መርነት (self-regulatory) ቁጥጥር ናቸው፡፡

በመጀመሪያው የመነሻ ራስ ቁጥጥር ደረጃ ተማሪዎች ስለመማር ችግሮቻቸው የመነሻ መረጃ ይሰበስባሉ፤ መነሻውንም ያመቻቻሉ፤ መምህሩ ደግሞ ብቃታቸውን እንዲገመግሙ ያግዛቸዋል፡፡ ከዚህ ቀጥለውም የመማር ግባቸውን ይጥላሉ፡፡

ሁለተኛው የተዋቀረ የራስ ቁጥጥር ደረጃ ተማሪዎች መምህሩ የሚያሳያቸውን መንገድ ተከትለው መሥራታቸውን የሚገመግሙበት ደረጃ ነው፡፡ መምህሩ ተማሪዎች የሚያከናውኗቸውን ተግባራት በዝርዝር ይወስናል፡፡ በዚህ መሠረትም ለብቻ ራሳቸውን መምራታቸውን ያሳያል፡፡ ተማሪዎች የተዋቀረ ራስ ቁጥጥር አሠራርን ካዳበሩ በኋላ ለብቻ ራሳቸውን መምራት ይጀምራሉ፡፡

ሦስተኛው ደረጃ የብቻ ራስ ቁጥጥር ሲሆን ይህም የተዋቀረ ራስ ቁጥር ልምዶችን ውስጣዊ እና የራስ ማድረግን የሚያሳይ ነው፡፡ መምህሩ ተደጋጋሚ የተዋቀረ ራስ ቁጥጥር ብልሃቶችን በማሳየት የራሳቸውን ብልሃት ማፍለቅ እንዲችሉ ይመራቸዋል፡፡ የመምህሩን ስልቶች ተከትለውም ተማሪዎች የመማር ዕድገታቸውን መምራት የሚያስችል ብልሃት ያዳብራሉ፡፡

አራተኛው የራስ-መርነት ቁጥጥር ሲሆን ይህም መምህሩ ከሚሰጣቸው ተግባራት ውጭ በሌሎች የመማር ተግባራት ላይ ራሳቸውን መምራት መቻል የሚያሳይ ነው፡፡ በዚህ ደረጃ መምህሩ ተማሪዎች ራሳቸውን የሚመሩበትን ብልሃትና ተግባራትን እንዲያዳብሩ ይጠይቃቸዋል፡፡ በተማሪዎች አሰራር ግን በቀጥታ ጣልቃ አይገባም፡፡ ራሳቸውን በአግባቡ እንዲመሩ ብቻ ያግዛል፡፡ መምህሩ የተማሪዎችን ራስ-መርነት ችሎታ ከገነባ በኋላ የመማር እድገታቸውንና ችግሮቻቸውን ይከታተላል፡፡ የራስ-መር ብልሃቶችን ከሚማሩት ትምህርት

ጋር የሚዛመድና የመማር ልምዳቸውን መሰረት በማድረግ የማስተማር ስነ-ዘዴውን ሊያሻሽል ይችላል።

## 2.8 የተዛማጅ ስራዎች ቅኝት

ይብሬ (2008)። በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የራስ-መር የመማር ብልሃት ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ያለውን ተዛምዶ መፈተሽ ዓላማ አድርጎ በዓይነታዊና መጠናዊ የጥናት ዘዴ በመጠቀም ባቀረበው ጥናታዊ ጽሑፍ የራስ-መር መማር ብልሃት ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር አወንታዊ ተዛምዶ እንዳለው አመላክቷል።

ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ራስ-መር የመማር ብልሃት ማጥናቱ ነው። ልዩነቱ ደግሞ ራስ-መር የመማር ብልሃትን ከተማሪዎች አንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ያለውን ተዛምዶ ያሳየበት ሲሆን ይህ ጥናት ግን ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ራስ-መር የመማር ብልሃት ከመተግበር አንፃር የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ያላቸውን አመለካከትና አተገባበር መፈተሽ ነው።

አብዮት (2005)። በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ራስ-መር የመማር ብልሃት ድርሰት ከመጻፍ ችሎታ ጋር ያለው ተዛምዶ መፈተሽ ዓላማ አድርጎ በዓይነታዊና መጠናዊ የጥናት ዘዴ በመጠቀም ባቀረበው ጥናታዊ ጹሑፍ ራስ-መር የመማር ብልሃት ድርሰት ከመጻፍ ችሎታ ጋር ከፍተኛ የሆነ ተዛምዶ እንዳለው አሳይቷል። ለተዛምዶውም ግብ መጣልና የመማር ብልሃትን መምረጥ በበለጠ ተነሳሽነትን ለመፍጠር ጉልህ ድርሻ እንዳላቸው አመላክቷል። እንዲሁም ለተማሪዎች ድርሰት የመጻፍ ችሎታ መጎልበት ራስ-መር የመማር ብልሃቶችን መጠቀም ከፍተኛ የሆነ አስተዋጽኦ እንዳለው አመላክቷል። በተጨማሪም ራስ-መር የመማር ብልሃት ድርሰት ከመጻፍ ችሎታ ጋር ከፍተኛ የሆነ ተዛምዶ ስላለው መምህራን ድርሰት በሚያስተምሩበት ጊዜ ተስማሚ የሆኑ የመማር ብልሃቶችን ቢጠቀሙ የተሻለ እንደሆነ ጥናቱ ያመለክታል።

ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ራስ-መር የመማር ብልሃት ማጥናቱ ነው። ልዩነቱ ደግሞ ራስ-መር የመማር ብልሃትን ከተማሪዎች የድርሰት መጻፍ ችሎታ ጋር ያለውን ተዛምዶ ያሳየበት ሲሆን ይህ ጥናት ግን ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ራስ-መር የመማር ብልሃትን ከመተግበር አንፃር የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ያላቸውን አመለካከትና አተገባበር መፈተሽ ነው።

ስሜነው (2002)። የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች የመማር ብልሃቶች አጠቃቀም ልዩነት ምርጫ ከፆታና ከትምህርት ውጤት አንፃር ያለውን ተዛምዶ መፈተሽ ዓላማ አድርጎ

በዓይነታዊና መጠናዊ የጥናት ዘዴ በመጠቀም ባቀረበው ጥናታዊ ጽሑፍ የመማር ብልሃት ከትምህርት ውጤት ጋር ተዛምዶ እንዳለው ሲያመለክት ከፆታ አንፃር ግን ተዛምዶ እንደሌለው አመላክቷል፡፡

ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ራስ-መር የመማር ብልሃት ላይ ማጥናቱ ነው ልዩነቱ ደግሞ የመማር ብልሃት ምርጫ ከፆታና ከትምህርት ጋር ያለውን ተዛምዶ ያሳየበት ሲሆን ይህ ጥናት ግን ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ራስ-መር የመማር ብልሃትን ከመተግበር አንፃር የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ያላቸውን  አመለካከትና አተገባበር መፈተሽ ነው፡፡

ይብሬ (2008) የጌትነትን (2006) ጠቅሶ እንደገለጸው ራስ-መር የመማር ብልሃት አጠቃቀምን ከቋንቋ ትምህርት ውጤት ጋር ያለውን ተዛምዶ መፈተሽ ዓላማ አድርጎ በዓይነታዊና መጠናዊ የጥናት ዘዴ በመጠቀም ባቀረበው ጥናታዊ ጽሑፍ ውጤታማ ተማሪዎች ውጤታማ ካልሆኑት የበለጠ ራስ-መር የመማር ብልሃትን የሚጠቀሙ መሆናቸውን ነው፡፡ ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው በራስ-መር የመማር ብልሃት ላይ ማጥናቱ ነው ልዩነቱ ደግሞ ራስ-መር የመማር ብልሃት አጠቃቀምን ከቋንቋ ትምህርት ውጤት ጋር ያለውን ተዛምዶ የፈተሸበት መሆኑ ነው ፡፡ ይህ ጥናት ግን ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ራስ-መር የመማር ብልሃትን ከመተግበር አንጻር የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ያላቸውን  አመለካከትና አተገባበር መፈተሽ ነው፡፡

Eric (2011) "የመማር ብቃትን በማሻሻል ረገድ ራስ-መር የመማር  ብልሃት ያለውን ሚና መፈተሽ" በሚል ዓላማ መጠናዊና ዓይነታዊ የጥናት ዘዴን በመጠቀም በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ጥናት አካሂደዋል፡፡ በጥናታዊ ጽሑፉ የተማሪዎች የመማር ተነሳሽነት፣ ግብ መጣልና የመማር ብልሃቶችን በመማር ብቃታቸው መሻሻል ጉልህ ሚና እንዳለው አመላክቷል፡፡ ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው በመማር ብልሃት ላይ ማጥናቱ ነው ልዩነቱ ደግሞ ራስ-መር የመማር ብልሃት ከብቃት ማሻሻል ጋር የተፈተሸበት መሆኑ ነው ፡፡ ይህ ጥናት ግን ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ራስ-መር የመማር ብልሃትን ከመተግበር አንፃር የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስለራስ-መር ያላቸውን  አመለካከትና አተገባበር መፈተሽ ነው፡፡

Robert (2003) "ራስ-መር የመማር ብልሃት እና የትምህርት መሻሻል (Academic performance) ያላቸው ግንኙነት መፈተሸ" ዓላማ አድጎ ዓይታዊና መጠናዊ የጥናት ዘዴን መሠረት በማድረግ ባጠናው ጥናት ራስ-መር ባህሪን ከመላበስ አንጻር በሂውማኒቲና በቴክኖሎጅ ተማሪዎች መካከል ልዩነት ታይቷል፡፡ የመማር አካባቢን መምራትና ተነሳሽነት ከትምህርት መሻሻል ጋር የጎላ ግንኙነት እንዳለው በጥናቱ አመላክቷል:: ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው በራስ-መር የመማር ብልሃት ላይ ማጥናቱ ነው፡፡ ልዩነቱ ደግሞ ራስ-መር

የመማር ብልሃት ከትምህርት ማሻሻል ጋር የፈተሸበት መሆኑ ነው ይህ ጥናት ግን ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ራስ-መር የመማር ብልሃትን ከመተግበር አንፃር የአማርኛ ያላቸውን አመለካከትና አተገባበር መፈተሽ ነው።

Sam & Faye (2009) በጥናታቸው ራስ-መር የመማር ብልሃቶችና ግብን ማወቅ የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች የትምህርት ውጤት የመተንበይ ብቃትን ያላቸውን ዝምድና መፈተሽ ዓላማ አድረጎ መጠናዊ የጥናት ዘዴን በመጠቀም ባቀረቡት ጥናት የተማሪዎች የቀደመ ውጤት ሁኔታና ራስ-መር የመማር ብልሃትን መጠቀም ውጤትን በመተንበይ ረገድ ጉልህ አስተዋጽኦ እንዳለው ሲያሳይ ግብን ማወቅ ግን ውጤትን ለመተንበይ ጉልህ ድረሻ እንደሌለው አሳይቷል። በዚህ ጥናትም በራስ መርነት፤ በተነሳሽነት እና በውጤት መካከል ጉልህ ተዛምዶ ታይቷል። ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው በራስ-መር የመማር ብልሃት ላይ ማጥናቱ ነው። ልዩነቱ ደግሞ ራስ-መር የመማር ብልሃት የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች ውጤታቸውን ከመተንበይ ብቃት ጋር የፈተሸበት መሆኑ ነው። ይህ ጥናት ግን ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ራስ-መር የመማር ብልሃትን ከመተግበር አንፃር የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ያላቸውን አመለካከትና አተገባበር መፈተሽ ነው።

ይብሬ (2008) Bucarest (1996) ጠቅሶ እንደገለጸው ጥናቱ በኢራን የከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች በቡድን በመክፍል ባጠናው ጥናት ስለራስ-መር የመማር ብልሃት ለአንደኛው ቡድን ስልጠና የሰጠ ሲሆን ለቀሪው ቡድን ደግሞ ምንም ዓይነት ትምህርት አልሰጠም። በጥናቱም ስልጠና የተሰጣቸው የአንብቦ መረዳት ችሎታቸውን ሲያዳብሩ ስልጠናው ያልተሰጣቸው ግን ችሎታቸው አልዳበረም። ከዚህ ላይ መረዳት የሚቻለው ራስ-መር የመማር ብልሃትና የቋንቋ ትምህርት ተዛማጅነት እንዳላቸው መገንዘብ ይቻላል። ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው በመማር ብልሃት ላይ ማጥናቱ ነው። ልዩነቱ ደግሞ ራስ-መር የመማር ብልሃት ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር የፈተሸበት መሆኑ ነው። ይህ ጥናት ግን ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ራስ-መር የመማር ብልሃትን ከመተግበር አንፃር የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ያላቸውን አመለካከትና አተገባበር መፈተሽ ነው።

በአጠቃላይ አጥኝው ባደረገው የቀደምት ጥናት ዳሰሳ ካነሳው ርዕስ ጋር ቀጥተኛ የሆነ ጥናት አላገኘም። ከላይ የተጠቀሱት ሁሉም ድርሳናት ራስ-መር የመማር ብልሃትን እና ከቋንቋ ትምህርት ጋር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መፈተሻቸው ከዚህ ጥናት ጋር ሲያመሳስላቸው፤ ይህ ጥናት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ራስ-መር የመማር ብልሃትን ከመተግበር አንፃር የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ያላቸውን አመለካከትና አተገባበር በመፈተሹ፣ በዘመን፣ በቦታ፣ በተጠኝዎች ብዛት ከጥናቶቹ ልዩነት አሳይቷል።

## ምዕራፍ ሶስት፤ የጥናቱ ንድፍና አካሄድ

### 3.1 የጥናቱ ንድፍ

የጥናቱ ዋና ዓላማ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ራስ-መር የመማር ብልሃትን ከመተግበር አንፃር የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ያላቸውን አመለካከትና አተገባበር መፈተሽ ነው፡፡ ጥናቱም መጠናዊ የምርምር ስልትን መሰረት በማድረግ ገላጭ ስታቲስቲክሳዊ የጥናት ንድፍን ተከትሏል፡፡ የጥናቱ መረጃም በፅሑፍ መጠይቅና በምልከታ ተሰብስቧል፡፡ የተገኘው መረጃም በመጠናዊ የትንተና ስልት ተተንትኖ በአይነታዊ ማብራሪያ ተጠናክሮ ቀርቧል፡፡

### 3.2 የጥናቱ አካላይ

የዚህ ጥናት አካላይ በደቡብ ጎንደር አስተዳደር ዞን በሊቦ ከምከም ወረዳ ከሚገኙት አራት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል አመቺ የናሙና ዘዴን በመጠቀም የተመረጡ ሶስት ትምህርት ቤቶች ሲሆኑ እነርሱም አዲስ ዘመን፣ ይፋግና አምቦ ሜዳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ናቸው፡፡ ከአራቱ ትምህርት ቤቶች መካከል ሚካኤል ደብር ሁለተኛ ደረጃ ያልተመረጠበት ምክንያት ከአጥኝው የስራ ቦታ ርቀት ያለው በመሆኑ ነው፡፡ የቦታው መራቅም አጥኝው መረጃ በሚሰበስብበት ወቅት የመረጃ ክፍተት ከማምጣቱም በተጨማሪ ከአጥኝው የገንዘብ አቅም በላይ ስለሚሆን ነው፡፡ የጥናቱ ትኩረትም የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስለ ራስ-መር የመማር ብልሃት ያላቸውን አመለካከት እና አተገባበር መፈተሽ ነው፡፡

### 3.3 የመምህራን ናሙና አመራረጥ

የመምህራን ናሙና የተመረጠው በሊቦ ከምከም ወረዳ በሚገኙ ሶስት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በአዲስ ዘመን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት16 መምህራን፣ በይፋግ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 8 መምህራንና በአምቦ ሜዳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 7 መምህራን በ2013 ዓ.ም ዘጠነኛ ክፍልን አማርኛ ቋንቋ የሚያስተምሩ ሰላሳ አንድ መምህራን በጠቅላይ ናሙና ዘዴ ተመርጠዋል፡፡ ሁሉም መምህራን የተመረጡበት ምክንያት ቁጥራቸው ብዙ ሲሆን የሚሰበሰበው መረጃ አስተማማኝ ይሆናል ብሎ በማሰብ ነው፡፡

#### 3.3.1 የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ራስ-መር የመማር ብልሃትን ከመተግበር አንፃር የ9ነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ያላቸውን አመለካከትና አተገባበር መፈተሽ ሲሆን ጥናቱ ያተኮረውም በደቡብ ጎንደር ዞን በሊቦ ከምከም ወረዳ

ካሉት አራት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል በሶስት ትምህርት ቤቶች ሲሆን እነርሱም አዲስ ዘመን፣ ይፋግና አምቦ ሜዳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ናቸው:: እነዚህ ትምህርት ቤቶች የተመረጡት በአመቺ (convenience sampling) የናሙና አመራረጥ ዘዴን በመጠቀም ነው:: በተጨማሪም አጥኚው የጥናቱን ዓላማ ለማሳካት መረጃዎችን በትክክልና በአስተማማኝ ሁኔታ ለማግኘትና ለመሰብሰብ አመች በመሆኑ ነው::

### 3.3.2 የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ

በአዲስ ዘመንና በይፋግ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ9ኛ፣ የ10ኛ፣ 11ኛ ክፍል እና የ12ኛ የክፍል ደረጃዎች የሚገኙ ሲሆን በአምቦ ሜዳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ግን የ11ኛና የ12ኛ የክፍል ደረጃዎች የሉም:: በመሆኑም በሁሉም ትምህርት ቤቶች ከሚገኙት የክፍል ደረጃዎች በዓላማ ተኮር የናሙና ዘዴ የ9ነኝ ክፍል መምህራን ተመርጠዋል:: በተጨማሪም የ9ኛ ክፍል መምህራን ቁጥር ከ10ኛ ክፍል የመምህራን ቁጥር ስለሚበልጥ የተጠኝዎች ቁጥር መብዛትም የሚሰበሰበውን መረጃ አስተማማኝነት ከፍ ያደርገዋል::

## 3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ

የጥናቱን ዓላማ መሰረት በማድረግ መረጃ እንዲያስገኙ የተመረጡት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የፅሑፍ መጠይቅና ምልከታ ናቸው::

### 3.4.1 የፅሑፍ መጠይቅ

በዚህ ጥናት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ራስ-መር የመማር ብልሃትን ከመተግበር አንፃር የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ያላቸውን አመለካከት መረጃ ለመሰብሰብ የፅሑፍ መጠይቅ ተዘጋጅቷል:: የፅሑፍ መጠይቁ ሊካርት ስኬል ሲሆን እያዳንዱ የፅሁፍ መጠይቅ አራት አራት አማራጮች አሉት:: እነሱም፦1. በጣም አልስማማም፣ 2. አልስማማም፣ 3. እስማማለሁ፣ 4. በጣም እስማማለሁ የሚሉ ናቸው:: አራት አማራጮች እንዲሆኑ የተደረገበት ምክንያት ያለው (1998) ተጠኚዎች "እርግጠኛ አይደለሁም" የሚለውን ጨምሮ አምስት አማራጮች ቢቀርቡላቸው ኃላፊነትና ጥንቃቄ በጎደለው ሁኔታ መሀለኛውን ወይም ሶስተኛውን የመምረጥ አዝማሚያ እንደሚያሳዩ በገለፁት መሰረት ይህ አማራጭ እንዲወገድ ተደርጓል::

የቀረቡት የፅሑፍ መጠይቆች ብዛት 20 (አባሪ አንድን ይመልከቱ) ሲሆኑ የፅሑፍ መጠይቆቹ የተዘጋጁትም Zimmerman (2002)፣ Azlina (2007) እና Eric (2011) ስራዎች የተማሪዎችን ራስ-መር የመማር ብልሃት ለመለካት በእግሊዘኛ ከተዘጋጁት ማሻሻያ በማድረግና ወደ አማርኛ ቋንቋ በመተርጎም ተዘጋጅቷል:: የፅሑፍ መጠይቆቹ የሁለተኛ

ድግሪ ባላቸው የአማርኛ ቋንቋ መምህራንና በአማካሪዬ ተገምግሞ በተሰጡት አስተያየቶች መሰረት እንደገና በማስተካከል ተዘጋጅቷል። የፅሑፍ መጠይቆቹም ከርዕሱ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማስማማት አገልግሎት ላይ ውሏል። የፅሑፍ መጠይቁን አስተማማኝነት ለማረጋገጥ ከጥናቱ ውጭ በሆኑ 10 የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተፈትሾ ውጤቱም በክሮምባች አልፋ ቀመር ተሰልቶ 0.87 ሁኖ ተመዝግቧል። ይህም ከ0.70 በላይ ስለሆነ ተቀባይነት አግኝቷል።

አጥኚው በተመረጡት ትምህርት ቤቶች ከመጋቢት 01/07–21/07/2013 ዓ.ም ድረስ መረጃውን ሰብስቧል። በመጀመሪያ በአዲስ ዘመን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከትምህርት ቤቱ አስተዳደርና የስራ ባልደረቦቹ መረጃ ለመሰብሰብ ፍቃደኝነታቸውን በመጠየቅ ፈቃድ አግኝቷል። በመቀጠልም ሁሉም መምህራን የሚገኙበትን ቀን ከትምህርት ቤቱ የክፍለ ጊዜ ሰሌዳ መረጃ በማየት ሁሉም መምህራን የሚገኙበት ቀን በ03/07/2013 መሆኑን አረጋግጧል። ይህም የተፈለገው ለሁሉም ተጠኝዎች ስለ ፅሑፍ መጠይቁ ዓላማ በአንድ ላይ ገለፃ ለማድረግ በማሰብ ነው። በመቀጠልም በ03/07/2013 ዓ.ም ለጥናቱ የተመረጡትን መምህራንን በዕረፍት ሰዓት ከአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል ቢሮ ላይ በመሰብሰብ ስለ ፅሑፍ መጠይቁ ዓላማ ለአምስት ደቂቃ ያህል ገለፃ ከተደረገ በኋላ ለእያዳንዱ ተጠኝ አንድ አንድ የፅሑፍ መጠይቅ ቅጽ በመስጠት ከትምህርት ክፍሉ በመውጣት ተራርቀው በፈለጉት ቦታ በመቀመጥ የፅሑፍ መጠይቁን እንዲሞሉ ተደርጓል። መራራቃቸውም በግድየለሽነት አንዱ የሌላውን መልስ እንዳይሞላ ያደርጋል ተብሎ በማሰብ ነው። በመጨረሻ የፅሑፍ መጠይቆቹን በመሰብሰብ ከአመሰገንኩ በኋላ የማስሞላት ሂደቱ ተጠናቋል።

ቀሪዎቹ የአጥኚው የጥናት ቦታዎች ይፋግ 2ኛ ደረጃ እና አምቦ ሜዳ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲሆኑ በእነዚህ ትምህርት ቤቶችም የፅሑፍ መጠይቆቹን ያስሞላው አጥኚው ነው። ይፋግ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከአጥኚው የሥራ ቦታ በ7 ኪሎ ሜትር ርቀት ውስጥ፣ አምቦ ሜዳ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ደግሞ በ25 ኪሎ ሜትር ርቀት ውስጥ ይገኛሉ። በቀን 10/07/2013 ዓ.ም ወደ ይፋግ፣ በቀን 17/07/2013 ዓ.ም ደግሞ ወደ አምቦ ሜዳ በአካል በመሄድ ለትምህርት ቤቶቹ አሥተዳደር፣ ለትምህርት ክፍሉ ተጠሪዎች እና በጊዜው ለተገኙት የ9ነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ራሱን በማስተዋወቅ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የፅሑፍ መጠይቅ እንዲሞሉለት ጠይቆ መልካም ፈቃድኝነታቸውን አግኝቷል። በመቀጠልም ሁሉም የይፋግ ተጠኝ መምህራን የሚገኙበት ቀን በ15/07/2013 ዓ.ም፣ የአምቦ ሜዳ ደግሞ በ21/07/2013 ዓ.ም መሆኑን አረጋግጦ ተመልሷል። ከዚያም በተጠቀሱት ዕለት ወደየትምህርት ቤቶቹ በመሄድ ሁሉንም ተጠኝዎችን ካገኘ በኋላ ከየትምህርት ክፍሉ ቢሮዎች ለአምስት ደቂቃ ስለፅሑፍ መጠይቁ ዓላማ ገለጻ ከተደረገ

በኋላ ለእያንዳንዱ ተጠኝ አንድ አንድ የፅሑፍ መጠይቅ ቅፅ በመስጠት ተራርቀው እንዲሞሉ በማድረግ በመጨረሻም የፅሑፍ መጠይቆቹን በመሰብሰብና በማመስገን የማስሞላት ሂደቱ ተጠናቋል፡፡ በፅሑፍ መጠይቅ አማካኝነት የተሰበሰበው መረጃም በነጠላ ናሙና ቲ.ቴስት (one sampling T test) ተሰርቶ በስታቲስቲክሳዊ ገላጭ ተብራርቷል፡፡

### 3.4.2 ምልከታ

በዚህ ጥናት ጥቅም ላይ የዋለው ሌላው የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያ ምልከታ ነው፡፡ ምልከታው ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ራስ-መር የመማር ብልሃትን ከመተግበር አንፃር የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሚያደርጉትን አተገባበር በክፍል ውስጥ ለመከታተል ጠቃሚ መረጃ መሰብሰቢያ በመሆኑ ነው፡፡ ምልከታው የተካሄደው የጥናቱ ተሳታፊ እንዲሆኑ በተመረጡት 9 የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ላይ ነው፡፡ የክፍል ውስጥ ምልከታ ለጥናቱ የመረጃ መሰብሰቢያ እንዲያገለግል የተመረጠበት ምክንያት በምልከታ የሚሰበሰብ መረጃ ከመጠይቅ በተሻለ ስለ መምህራን ትክክለኛ ባህሪ ማለትም በክፍል ውስጥ የሚያካሂዱትን የመማር ማስተማር ሂደት የራስ-መር የመማር ብልሃቶችን አተገባበር የሚያከናውኑትን እንቅስቃሴ በምን መልኩ እየተገበሩ እንደሆነ ለማወቅ በተጨባጭ ለማየትና ቀጥተኛ መረጃ ለማግኘት እንደሚያስችል በመታመኑ ነው፡፡

ምልከታውን በተገቢው መንገድ ለማከናወን ይቻል ዘንድ ስለራስ-መር የክፍል ውስጥ አተገባበር መደበኛ የሆነ ቼክ ሊስት ተዘጋጅቷል፡፡ ቼክ ሊስቱ የተዘጋጀው Zimmerman (2002)፣ Eric (2011) Torrano &Torress (2004) እና Lapan (2008) ስራዎች በራስ-መር የመማር ብልሃት መምህራን በክፍል ውስጥ ያላቸውን አተገባበር ለመለካት በእንግሊዘኛ ከተዘጋጁት ቼክ ሊስቶች ወደ አማርኛ ቋንቋ በመቀየርና ጥናቱ ይዞት ከተነሳው መሪ ጥያቄዎች አንጻር  መረጃ ለመሰብስብ እዲያመች በማድረግ ተዘጋጅቷል፡፡ የመረጃውን አስተማማኝነት ለማረጋገጥ ከጥናቱ ውጭ በሆኑ በአዲስ ዘመን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከሚያስተምሩ 10 የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተፈትሾ ውጤቱም በአማካይ 61.02 ሆኗል፡፡ ይህም በአማካይ ከ50 በላይ በመሆኑ ተቀባይነት አግኝቷል፡፡ ይህን በመጠቀም መምህራን በክፍል ውስጥ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ራስ-መር የመማር ብልሃትን ከመተግበር አንፃር ያላቸውን አተገባበር ምን እንደሚመስል በምልከታው ሂደት ተቃኝቷል፡፡ ምልከታው የተካሄደው በአጥኚው ነው፡፡

ምልከታው የፅሑፍ መጠይቁን ከሞሉት 31 የ9ነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን መካከል ከአዲስ ዘመን 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የፅሑፍ መጠይቁን ከሞሉት 16 መምህራን መካከል 3 መምህራንን፣ ከይፋግ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የፅሑፍ መጠይቁን

ከሞሉት 8 መምህራን መካከል 3 መምህራንን እና ከአምቦ ሜዳ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የፅሑፍ መጠይቁን ከሞሉት 7 መምህራን መካከል 3 መምህራንን ለመምረጥ ለእያንዳንዳቸው ሦስት ሦስት ወረቀት ከአንድ እስከ ሦስት ቁጥር ያለው ሌላውን ደግሞ ዜሮ በማድረግ ወረቀቶቹን በመጠቅለል ዕጣ እንዲያወጡ በማድረግ ቁጥሩ የደረሳቸው ለምልከታ ተመርጠዋል፡፡ እያንዳንዱ ተጠኚ ከ01/08—21/10/2013 ዓ.ም ባለው ጊዜ ሦስት ዙር ምልከታ በአጥኚው ተካሂዷል፡፡ ይህም 27 ጊዜ ምልከታ ተካሂዷል ማለት ነው፡፡ እያንዳንዱ ምልከታ የ40 ደቂቃ የጊዜ እርዝማኔ ነበረው( አባሪ ስድስትን ይመልከቱ)፡፡

በመጀመሪያ በአዲስ ዘመን 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ምልከታው የተከናወነው ከ01/08—09/10/2013 ዓ.ም በነበረው ጊዜ ነበር፡፡ የመጀመሪያው ዙር ምልከታ በ01/08/2013 ዓ.ም የተከናወነ ሲሆን አጥኚው በዚሁ ዕለት ቀደም ብሎ በቦታው በመገኘት ተጠኚ መምህራንን ስንተኛው ክፍለ ጊዜ እና የትኛው ክፍል እንዳላቸው በመጠየቅ ተጠኚ አንድ በሁለተኛው ክፍለ ጊዜ 9ነኛH ተጠኚ ሁለት በአራተኛው ክፍለ ጊዜ 9ነኛD፣ ተጠኚ ሦስት በስድስተኛው 9ነኛY መሆኑን አረጋግጧል፡፡

የሁለተኛው ዙር ምልከታ የተከናወነው በ22/08/2013 ዓ.ም ሲሆን በዚህ ዕለትም ተጠኚ መምህራንን ቀደም ብሎ በማግኘት የዕለቱን ክፍለ ጊዜ እና ክፍሉን በመጠየቅ ተጠኚ አንድ በሁለተኛው 9ነኛJ፣ ተጠኚ ሁለት በሦተኛው 9ነኛC፣ ተጠኚ ሦስት በአምስተኛው 9ነኛW መሆኑን አረጋግጧል፡፡

የሦስተኛው ዙር ምልከታ የተከናወነው በ09/10/2013 ዓ.ም ሲሆን በዚህ ቀንም አጥኚው ተጠኚዎችን ቀደም ብሎ በማግኘት ተጠኚ አንድ በአምስተኛው 9ነኛH፣ ተጠኚ ሁለት በሦተኛው 9ነኛI፣ ተጠኚ ሦስት በአምስተኛው 9ነኛW የሚገቡበት ክፍል መሆኑን አውቋል፡፡

ከላይ የተዘረዘሩትን መረጃዎች መሠረት በማድረግ በሦስቱም ዙር ምልከታ አጥኚው ጊዜውን በመጠበቅ የምልክታ ቅፅና የማስታዎሻ ደብተር በመያዝ ወደ ክፍል አብሮ በመግባት የመማር ማስተማ ተግባሩ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ እስከሚጠናቀቅ ድረስ በክፍል ውስጥ በንቃት በምልከታው ቅፅ ላይ ያሉትን የራስ-መር ተግባራት መተግበራቸውንና አለመተግበራቸውን መረጃዎችን በመሰብሰብ ሥራውን አጠናቋል፡፡ በመጨረሻም ተጠኚዎች በነበረው ቆይታ ላደረጉት ቀና ትብብር በማመስገን መረጃ የመሰብሰብ ሂደቱ ተጠናቋል፡፡

ሁለተኛው የአጥኚው የጥናት ቦታ ይፋግ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲሆን በዚህ ትምህርት ቤትም የምልከታ ተግባር የተከናወነው ከ11/08–17/10/2013 ዓ.ም ባለው ጊዜ ነበር፡፡

የመጀመሪያው ዙር ምልከታ የተከናወነው በ11/08/2013 ዓ.ም ሲሆን በዚሁ ዕለት አጥኚው በቦታው በመገኘት ለምልከታ ተግባር በዕጣ የመረጣቸውን 3 የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በማግኘት በዕለቱ ያላቸውን ክፍለ ጊዜ እና ክፍል በመጠየቅ ተጠኚ አንድ በሁለተኛ 9ነኛK፣ ተጠኚ ሁለት በአምስተኛው 9ነኛE፣ ተጠኚ ሦስት በስድስተኛው 9ነኛO መሆኑን አረጋግጧል።

የሁለተኛው ዙር ምልከታ የተከናወነው በ29/08/2013 ዓ.ም ሲሆን በዕለቱም ትምህርት ከመጀመሩ በፊት ተጠኚ መምህራንን በማግኘት ተጠኚ አንድ በአንደኛው 9ነኛL፣ ተጠኚ ሁለት በሁለተኛው 9ነኛF፣ ተጠኚ ሦስት በአራተኛው 9ነኛN የሚገቡበት ክፍል መሆኑን አውቋል።

የሦስተኛው ዙር ምልከታ የተከናወነው በ17/10/2013 ዓ.ም ነበር። በዚሁ ዕለትም እንደተለመደው ተጠኚ መምህራንን ትምህርት ከመጀመሩ በፊት ቀደም ብሎ በማግኘት በዕለቱ የሚገቡበትን ክፍል ተጠኚ አንድ በሁለተኛው 9ነኛL፣ ተጠኚ ሁለት በአምስተኛው 9ነኛE፣ ተጠኚ ሦስት በስድስተኛው 9ነኛM መሆኑን አረጋግጧል።

በሦስቱም ዙር የምልከታ ጊዜ ከላይ በተገለፀው መረጃ መሠረት አጥኚው እያንዳንዱን ክፍለ ጊዜ እና ክፍል መሠረት በማድረግ ከተጠኚ መምህራን ጋር ወደ ክፍል አብሮ በመግባት የመማር ማስተማሩ ተግባር ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ እስኪጠናቀቅ ድረስ የራስ-መር ተግባራት መተግበርና አለመተግበራቸውን በንቃት በመከታተል ተገቢውን መረጃ በመሰብሰብ ተግባሩን አከናውኗል። በመጨረሻም ተጠኚ መምህራን ጥናቱ ከተጀመረ አንስቶ እስኪጠናቀቅ ድረስ ላደረጉት ቀና ትብብር በማመስገን በትምህርት ቤቱ የነበረውን ቆይታ አጠናቋል።

ሶስተኛው የአጥኚው የጥናት ቦታ አምቦ ሜዳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲሆን በዚህ ትምህርት ቤት የምልከታ ተግባር የተከናወነው ከ05/09–21/10/2013 ዓ.ም ባለው ጊዜ ነበር።

የመጀመሪያው ዙር ምልከታ የተከናወነው በ05/09/2013 ዓ.ም ሲሆን በዚሁ ዕለት አጥኚው በቦታው በመገኘት ለምልከታ በዕጣ የመረጣቸውን 3 የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የዕለቱ ትምህርት ከመጀመሩ በፊት በማግኘት የሚያስተምሩበትን ክፍል ተጠኚ አንድ በአንደኛው ክፍለ ጊዜ 9ነኛB ተጠኚ ሁለት በሶስተኛው ክፍለ ጊዜ 9ነኛF ተጠኚ ሶስት በአምስተኛው ክፍለ ጊዜ 9ነኛJ መሆኑን አረጋግጧል።

የሁለተኛው ዙር ምልከታ የተከናወነው በ27/09/2013 ዓ.ም ሲሆን በዕለቱም ትምህርት ከመጀመሩ በፊት ተጠኝ መምህራንን በማግኘት ተጠኝ አንድ በሁለተኛው 9ነኛB፣ ተጠኝ ሁለት በአራተኛው 9ነኛG፣ ተጠኝ ሦስት በሶስተኛው 9ነኛJ የሚገቡበት ክፍል መሆኑን አውቋል፡፡

የሦስተኛው ዙር ምልከታ የተከናወነው በ21/10/2013 ዓ.ም ነበር፡፡ በዚሁ ዕለትም እንደተለመደው ተጠኝ መምህራንን ትምህርት ከመጀመሩ በፊት ቀደም ብሎ በማግኘት በዕለቱ የሚገቡበት ክፍል ተጠኝ አንድ በሶስተኛው 9ነኛA፣ ተጠኝ ሁለት በሁለተኛው 9ነኛH፣ ተጠኝ ሦስት በአራተኛው 9ነኛJ መሆኑን አረጋግጧል፡፡

በሦስቱም ዙር የምልከታ ጊዜ ከላይ በተገለፀው መረጃ መሠረት አጥኚው እያንዳንዱን ክፍለ ጊዜ እና ክፍል መሠረት በማድረግ ከተጠኝ መምህራን ጋር ወደ ክፍል አብሮ በመግባት የመማር ማስተማሩ ተግባር ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ እስኪጠናቀቅ ድረስ የራስ-መር ተግባራት መተግበርና አለመተግበራቸውን መረጃውን ሰብስቧል፡፡ በመጨረሻም ተጠኝ መምህራን ጥናቱ ከተጀመረ አንስቶ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ላደረጉት ቀና ትብብር በማመስገን በትምህርት ቤቱ የነበረውን ቆይታ አጠናቋል፡፡

## 3.5 የመረጃ አተናተን ዘዴ

በፅሑፍ መጠይቅ ከተጠኚዎች የተገኘው መረጃ ከመተንተኑ በፊት መልሶቹ በትክክል ተጠየቃዊ በሆነ መንገድ መሞላታቸው ተጣርቶ መረጃው ለትንተና በሚያመች መልኩ ኮድ ተደርጎ በውጤት መመዝገቢያ ሰንጠረዥ (ኮድ ሽት) ላይ ሰፍሯል (አባሪ ሶስትን ይመልከቱ)፡፡ በመጨረሻም ወደ ትንታኔ ከመገባቱ በፊት በተሞላው መረጃ ላይ የማጣራት ተግባር ተከናውኗል፡፡

በተጠኚዎቹ የተገኘው መረጃም በስታቲስቲክሳዊ ገላጭ የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎች ተተንትኗል፡፡ ይህውም ተማሪዎች ራስ-መር እንዲሆኑ ለማድረግ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ያላቸውን አመለካከት ለማወቅ በፅሑፍ መጠይቅ የቀረቡት ጥያቄዎች 20 ሲሆኑ (አባሪ ሁለትን ይመልከቱ) መረጃውም የአማካይ የመቁረጫ ነጥብ 2.5 መነሻ በማድረግ ነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ቀመር (one sampling t-test) ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ የመምህራንን አተገባበር ደግሞ በምልከታው የተገኘው መረጃ ጭብጦችን ሊያሳይ በሚችል መልኩ በጭብጥ በጭብጥ በየዝምድናቸው ተመድበዋል፡፡ በመቀጠል ከምድቡ የወጡ ጭብጦች በመቶኛ ተሰልቶ ተተንትኗል፡፡

በአጠቃላይ በሁለቱ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የተገኙ መረጃዎችን በመለየትና በመመደብ በአይነት ወይም በጭብጥ ስሜት ሊሰጥ በሚችል መልኩ የምርምሩን ጥያቄዎች መነሻ በማድረግ ተተንትኖ ተብራርቷል፡፡

# ምዕራፍ አራት፤ የጥናቱ መረጃ ትንተና እና ማብራሪያ

## 4.1 የጥናቱ መረጃ ትንተና

የዚህ ጥናት አንደኛው መሰረታዊ ጥያቄ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ራስ-መር የመማር ብልሃትን ከመተግበር አንፃር የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ያላቸው አመለካከት ምን ይመስላል? የሚል ሲሆን ይህን ጥያቄ ለመመለስም ስራ ላይ የዋለው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ በመምህራን የሚሞላ የፅሑፍ መጠይቅ ነው። መጠይቁም 20 ጥያቄዎችን የያዘ ነው። እያዳንዱ ጥያቄም አራት አራት አማራጮች ያሉት ሲሆን 1 በጣም አልስማማም፣ 2 አልሰማማም፣ 3 እሰማማለሁ እና 4 በጣም እስማማለሁ የሚሉ ናቸው። ተጠኝዎች ለእያዳንዱ ጥያቄ የሰጡት ምላሽ በፐርሰት፤ የፅሑፍ መጠይቁ ውጤት ደግሞ በነጠላ ናሙና ቲ.ቴስት (one sampling t. test) ተብራርቶ ውጤቱም እንደሚከተለው በሰንጠረዥ ተመልክቷል

ሰንጠረዥ 4.1 የፅሑፍ መጠይቁን ምላሽ በፐርሰንት የሚያሳይ ሰንጠረዥ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | 1 | | 2 | | 3 | | 4 | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 1 | ራስ-መር፡-ራስን የመምራት፣ የመቆጣጠር እና የማዘዝ ሂደት መሆኑን እገነዘባለሁ፤ | | | | | 20 | 64.5 | 11 | 35.5 |
| 2 | ራስ-መር መማር ለተማሪዎች አስፈላጊ ነው ብየ አምናሁ፤ | | | | | 15 | 48.4 | 16 | 51.6 |
| 3 | መምህራን ለተማሪዎቻቸው በመማር ሂደት የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች ለመፍታት የሚያስችሉ ብልሃቶችን ማስገንዘብ ይጠበቅባቸዋል፤ | | | | | 18 | 58.1 | 13 | 41.9 |
| 4 | ተማሪዎች ራስ-መር እንዲሆኑ የመምህራን ድርሻ የጎላ መሆኑን እገነዘባለሁ፤ | | | | | 22 | 71 | 9 | 29 |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 5 | ተማሪዎች በራሳቸው ተነሣሽነት እንዲማሩ መደረግ አለበት፤ | | | | | 19 | 61.3 | 12 | 38.7 |
| 6 | ተማሪዎች በራሳቸው ተነሣሽነት የሚማሩበትን ብልሃት እንዲያዳብሩ መታገዝ አለባቸው፤ | | | | | 18 | 58.1 | 13 | 41.9 |
| 7 | ተማሪዎች ራሳቸውን እንዲቆጣጠሩ እገዛ ያስፈልጋቸዋል፤ | | | | | 21 | 67.7 | 10 | 32.3 |
| 8 | ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ተነሳሽነታቸው እንዲጨምር የተለያዩ ስልቶችን መጠቀም ያስፈልጋል፤ | | | 1 | 3.2 | 16 | 51.6 | 14 | 45.2 |
| 9 | ተማሪዎች በራሳቸው ተነሳሽነት ቢማሩ ውጤታማ ይሆናሉ፤ | | | 1 | 3.2 | 14 | 45.2 | 16 | 51.6 |
| 10 | ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ግባቸውን በራሳቸው እንዲጥሉ ማድረግ አስፈላጊ ነው፤ | | | 1 | 3.2 | 18 | 58.1 | 12 | 38.7 |
| 11 | ተማሪዎች ግባቸውን ለማሳካት ሊገጥሙ የሚችሉ ችግሮችን በመለየት የመፍትሄ ብልሃቶችን ማቀድ ይጠበቅባቸዋል፤ | | | 1 | 3.2 | 16 | 51.6 | 14 | 45.2 |
| 12 | ራስ-መር ተማሪዎች ከግባቸው አንፃር ራሳቸውን እንዲገመግሙ፣ መሻሻላቸውን እንዲያዩ፣ መሻሻላው ደግሞ ርካታቸውንና ተነሳሽነታቸውን እንዲጨምር ያደርጋል፤ | | | 1 | 3.2 | 22 | 71 | 8 | 25.8 |
| 13 | ራስ መር መማር የተማሪዎችን የመማር ኃላፊነትና በራስ መተማመንን ከፍ በማድረግ | | | | | 22 | 71 | 9 | 29 |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | በፍጥነት እንዲማሩ ያደርጋቸዋል፤ | | | | | | | | |
